# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 247 ግንቦት 7 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡-ዳኜ አበራ

## አድናቆት የሚገባቸውን ሰዎች ማክበር ልምዳችን ሊሆን ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገሩ

### - ዩኒቨርሲቲው ለጣሊያኑ ሳሊኒና ለናይጀሪያዊው አኪንዊሚ አዴሲና የክብር ዶክትሬት ሰጠ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- አድናቆት የሚገባቸውን ሰዎች ማክበር ልምዳችን ሊሆን ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናገሩ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለጣሊያኑ ሳሊኒ /ዊ ቢውልድ/ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ፔትሮ ሳሊኒና ለአፍሪካ ልማት ባንክ ግሩፕ ፕሬዚዳንት ናይጀሪያዊው አኪንውሚ አዴሲና የክብር ዶክትሬት ሰጥቷል።

በወዳጅነት አደባባይ በተካሄደው መርሃ ግብር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለተሸላሚቹ የክብር ዶክትሬቱን አበርክተዋል።

ታዋቂው አርክቴክት ፍራንክ ራይት እንዳለው፤ የአንድ የሰው ልጅ ባህሉ የሚለካው በሚሰጠው አድናቆት መጠን ነው። ስለሆነም ክብር የሚገባቸውን ሰዎች ማክበር ልምዳችን ሊሆን ይገባል፤ ወጣቶችም ብዙ ከሰሩ ሰዎች ዕውቀትና ልምድን ከመቅሰም ባለፈ አድናቆትና ማክበርን መማር አለባቸው ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ክብር ለሚገባቸው ሁለቱ የግብርና ኢኮኖሚክስና ኢንጂነሪንግ ሰዎች ክብር መስጠቱ አግባብ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ለሁለቱም ተሸላሚዎች ይህን ክብር ማግኘት ቀላል አይደለም፤ አድናቆቱን ለማግኘት በተሰማሩባቸው ዘርፎች ውጤታማ በመሆን ብዙ ደክመዋል። በየዘርፋቸው

**አድናቆት የሚገባቸውን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



## “ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁላችንንም ጥረትና ትብብር ትፈልጋለች”

### - ድምጻዊ አቡሽ ዘለቀ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ዘላቂ ሰላምና ዕድገት ለማምጣት ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁላችንንም ጥረትና ትብብር ትፈልጋለች ሲል ድምጻዊ አቡሽ ዘለቀ ገለጸ፡፡

ድምጻዊ አቡሽ ዘለቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፀው፤ኢትዮጵያን አላወቅናትም እንጂ ብናውቃትና ብትገባን ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የምትተርፍ ሀገር ነች፡፡ ኢትዮጵያ በሃይማኖቶች መከባበርና መቻቻል ላይ የተለየ ታሪክ አላት፤ ይህን የቆየ መልካም እሴት ለማጠልሸት የክፋት ስራቸውን ለሚሰሩ ሰዎች እጅ መስጠት አያስፈልግም፡፡ ዘላቂ ሰላምና ዕድገት ለማምጣት ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁላችንንም ጥረትና ትብብር ትፈልጋለች ብሏል፡፡

ሀገር ማጣት ህመሙ ከባድ ነው፤ እኛ ሀገር ስላለችን ያንን ባንረዳም ብዙ ህዝቦች ሀገር አጥተው ሲንከራተቱ እያየን ነው ያለው ድምፃዊው፤ እኛም እኩይ ዓላማ ባላቸው ግለሰቦች በሃይማኖትና በብሄር ሽፋን በሚከሰቱ ግጭቶች የዚያ ገፈት ቀማሽ እንዳንሆን በሀገር ጉዳይ ላይ በአንድነትና በመተባበር መስራት ይኖርብናል ሲል ተናግሯል፡፡

ሁሉም ወደ ልቦናው ተመልሶ የምንወዳትን ሀገራችንን ልንጠብቅ ይገባል የሚለው ድምጻዊ አቡሽ፤በአገሪቷ የሚስተዋሉ ሃይማኖትንና ብሄርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ተረባርበን አፋጣኝ መፍትሄ ልንሰጣቸው ይገባል ብሏል፡፡

አንድነትን በማስቀደምና ለሀገር ክብር በመኖር ሁሉም ወደ ልቦናው ተመልሶ ለዘላቂ ሰላምና ዕድገት መስራት እንደሚያስፈልግ ገልጾ፤ሁላችንም የየራሳችንን አስተዋጽኦ ካደረግን ሁሉም ችግሮች በቀላሉ መፍትሄ

**“ሀገራችን ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## መንግሥት አፍራሽ ተልዕኮ በማንገብ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ

### . የኑሮ ውድነትን ለማቃለል የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ተነድፎ እየተሰራ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው አፍራሽ ተልዕኮ በማንገብ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቀ።እየተስተዋለ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቅረፍ መንግሥት የአጭርና የረጅም ዕቅድ ተነድፎ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በአገራዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ መንግሥት በመላ አገሪቱ ሰላምን ለማስፈን በሰራው ተግባር በአብዛኛው የአገሪቱ አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም ማስፈን ተችሏል። መንግሥት ለሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው አፍራሽ ተልዕኮ በማንገብ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል።

ለሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው አፍራሽ ተልዕኮ



**ዶክተር ለገሰ ቱሉ**

በማንገብ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ መንግሥት የሚወስደውን እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል የገለጹት ለገሰ ቱሉ (ዶክተር)፤ የግጭት ነጋዴዎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ መንግሥት ያስጠነቅቃል። በተለያየ መንገድ የሕዝብን ሰላም የሚያውኩ ቡድኖች ከአሸባሪዎቹ ሸኔና ሕወሓት ተለይተው የማይታዩ በመሆናቸው እርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት መንግሥት ለየትኛውም አይነት የጦርነት ትንኮሳ ምላሽ ለመስጠት የጸጥታ ኃይሉ ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ መልኩ ዝግጁና አስተማማኝ በሆነ ቁመና ላይ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ለገሰ ገለጻ፤ መላው የጸጥታ መዋቅር በወሰደው የተቀናጀ ኦፕሬሽን የአገሪቷን ጸጥታ ለማወክ ከሰሞኑ ብቻ በአዲስ አበባ፣ በሶማሌ ክልል በተለያዩ ዞኖች፣ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሀረርጌና በምስራቅ ባሌ ለሽብር ተግባር የተሰማሩ 45 የአልሸባብ የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ነው፡፡

ከሽብር ቡድኑ አባላት 105 ክላሽ እንኮቭ ጠመንጃ፣

**መንግሥት አፍራሽ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**







ዜና



## አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ለግብርና ሥራውም ይሁን ለሰብአዊ አቅርቦቱ እንቅፋት ሆኖ መቀጠሉ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ክልል ለግብርና ሥራውም ይሁን ለሰብአዊ አቅርቦቱ እንቅፋት ሆኖ መቀጠሉ ተገለጸ። ቡድኑ በአጎራባች ክልሎች ዳግም ወረራ ለመፈፀም እያደረገ ያለው ዝግጅት ከስህተቱ አለመማሩንና በፀረ- ህዝብነቱ መቀጠሉን የሚያረጋግጥ መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አገኘው ተሻገር ተናገሩ።

አሸባሪ ቡድኑ ለትግራይ ክልል ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታ ተደራሽ እንዳይሆንና የግብርና ስራውን ለማስተጓጎል የሚያደርገውን ሰብአዊነት የጎደለው ተግባር እንዲያቆም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጫና እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አገኘው ተሻገር፤ አሸባሪው ሕወሓት "እኔ ብቻ የማልመራት ኢትዮጵያ ትፍረስ" ብሎ በመነሳት በሕዝቦች ትግል እውን የሆነውን ለውጥ ለማደናቀፍ እየጣረ መሆኑን ገልጸዋል።

አሸባሪ ቡድኑ ለዳግም ጦርነት በግልጽ እየተዘጋጀ መሆኑን ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች ጭምር እያጋለጡ መሆኑን ጠቅሰው "ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል እወርዳለሁ" የሚል የጥፋት አጀንዳውን ቀጥሎበታል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት የሰብአዊ ድጋፍና የግብርና ሥራ እንዳይስተጓጎል መንግሥት ያወጀውን የተኩስ አቁም ለዳግም ጥፋት እየተዘጋጀበት መሆኑንም ገልጸዋል።

በአማራ፣አፋርና ትግራይ ክልሎች መንግሥት የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽ በማድረግ ላይ ቢሆንም አሸባሪ ቡድኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች የማስተጓጎል ተግባር ስለመፈጸሙ ጠቅሰዋል።

ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም የተሳለጠ ሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽ ማድረግ እንዲችሉ መንግሥት በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

ይሁን እንጂ አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ አጎራባች ክልሎች ዳግም ወረራ ለመፈጸም በዝግጅት ላይ መሆኑን በአደባባይ በመግለፅ ላይ ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች ጭምር እያጋለጡ መሆኑን አቶ አገኘሁ ገልጸዋል።

በመሆኑም የአሸባሪ ቡድኑ እንቅስቃሴ በተደጋጋሚ ከስህተቱ የማይማርና በፀረ-ሕዝብ ተግባሩ መቀጠሉን ማረጋገጫ ነው ብለዋል።


በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች ለአርሶ አደሩ የዘርና የማዳበሪያ አቅርቦት ተደራሽ በመደረግ ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ በትግራይ አካባቢ ግን ለግብርና ሥራውም ይሁን ለሰብአዊ አቅርቦቱ አሸባሪው ሕወሓት እንቅፋት ሆኖ ቀጥሏል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ከህጻናት እስከ አዛውንት ዜጎችን ለጦርነት እያስገደዳቸው መሆኑን ጠቁመው፤የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድርጊቱን ሊቃወመውና በግልጽ ሊያወግዘው ይገባል ነው ያሉት።

ለትግራይ ክልል ሕዝብ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲደርስ መንግሥት እያደረገ ያለውን ጥረትም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሊደግፈው እንደሚገባ ኢዜአ ዘግቧል።

## አርብቶ አደሩ ተገቢውን ትኩረት ተነፍጎት በመቆየቱ በሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ተሳትፎው ውስን መሆኑ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- ከለውጡ በፊት ያሉ መንግሥታት ለአርብቶ አደሩ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው በሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ መጫወት ያለበትን ሚና አለመጫወቱን በሰላም ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ሻንቆ ደለለኝ አስታወቁ።

ላንድ ቱ ላይፍና የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደር ልማት ቢሮ የአርብቶ አደር ልማት ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂን አስመልክቶ በጋራ ባዘጋጁት የማነቃቂያ ወርክሾፕ ላይ በሰላም ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ሻንቆ ደለለኝ እንደገለጹት፤ አርብቶ አደሩ ትኩረት አልተሰጠውም፤ ሁሉም ፕሮግራሞች ከመሀል ወደ ዳር እንጂ ከአርብቶ አደሩ መንደር ወደ መሃል ሀገር መስራት ይቻላል ተብሎ አልታሰበም። ይህ ደግሞ አርብቶ አደሩ በሀገረ ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ሊጫወት የሚገባውን ሚና እንዳይጫወት አድርጎታል።

በድንበር ያሉ አርብቶ አደሮች ከማሀል አገር ይልቅ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ጠንካራ የሆነ የንግድ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸው፤ በዚህ ሳቢያ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ ገቢ ከአርብቶ አደሩ ስታጣ መቆየቷን ተናግረዋል።

የአርብቶ አደሩን ሕይወት በዘላቂነት ለማሻሻል የፌዴራል መንግሥቱ ከፍተኛ ሚና መጫወት አለበት ያሉት አቶ ሻንቆ፤ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ማድረግ፣ ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት የአርብቶ አደሩን ሕይወት ማሻሻልና የአቅም ግንባታን ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብለዋል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የአርብቶ አደሩን አኗኗር በመረዳት አቅሙን በመገንባት ረገድ በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደር ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሮባ ቱርቼ በበኩላቸው፤ አዲሱ ፖሊሲ የአርብቶ አደሩን ሕይወት በዘላቂነት ለመቀየር እንደ ግብአት የሚያገለግል ቢሆንም በራሱ ለውጥ አያመጣም። በየጊዜው በአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰውን ችግር ለመቅረፍ አመላካች የመፍትሔ አቅጣጫዎች አሉት ብለዋል።

ፖሊሲው በትክክል እንዲተገበር የአርብቶ አደሩ ሕይወት እንዲሻሻል የሚመለከታቸው ተቋማት እንዲያውቁና ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ እንዲያመጣ እንደሚደረግ አመልክተው፤ በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ በየጊዜው ድርቅ ይከሰታል፤ ይህን ለመቅረፍ ክልሉ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

የከብቶችን መኖ በመስኖ የማልማት ስራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ሮባ፤ የኩሬ ውሃን በማስፋፋት በየጊዜው የሚደርሰውን ድርቅ ለመቅረፍ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በቦረና አካባቢ የመስኖ ውሃ በመጠቀም ከፍተኛ የሆነ የከብቶች መኖ እየለማ መሆኑን ጠቁመዋል። ውሃን በማቆር፣ ትንንሽ ግድቦችን በመስራትና የኩሬ ውሃዎችን የማስፋፋት ስራ እየተካሄደ በመሆኑ በቀጣይ የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል ከፍተኛ ስራ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

## በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ የተጎዱ አርሶ አደሮችን ቤት ሰርተው አስረከቡ

**ሙሉቀን ታደገ**



ጋሸና ፡- በዋድላ ወረዳ በጋሸና ግንባር አጤ ውሃ ምሽግ አካባቢ በጦርነቱ ምክንያት ቤታቸው ለፈረሰባቸው የአርሶ አደሮች ቤቶችን ሰርተው ማስረከብ መጀመራቸውን በአሜሪካን ሃገር ኑሯቸውን ያደረጉት በጎ አድራጊ አቶ ጥበበ እሸቱ ገለጹ።

በትናትናው ዕለት በጋሸና ግንባር አጤ ውሃ ምሽግ አካባቢ በነበረው የቤት ማስረከብ ስነ ስርዓት ላይ መልዕክት ያስተላለፉት አቶ ጥበበ እሸቱ እንደተናገሩት በዋድላ ወረዳ ጋሸና ግንባር አጤ ውሃ ምሽግ አካባቢ ከአምስት ጊዜ በላይ ጦርነት ተካሂዷል። በጦርነቱም ከ2 ሺህ 787 በላይ ቤቶች ወድመዋል። በዚህም በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ አርሶ አደሮች ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው በዋሻ ለመኖር ተገደዋል።

አሜሪካን በነበሩበት ወቅት ቤታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው አርሶ አደሮች በዋሻ ለመኖር መገደዳቸውን በዘጋቢ ቪዲዮዎች እንደተመለከቱ የተናገሩት አቶ ጥበበ፤ በዚህ ቁጭት በጦርነት የተጎዱ አርሶ አደሮችን ቤት ለመስራት መነሳሳታቸውን ገልጸዋል።

አሁን ላይ ክረምት እየደረሰ ነው። እነኝህን አርሶ አደሮች ክረምት ከመድረሱ በፊት ቤታቸውን በመስራት እና በመጠገን ወደ ቤታቸው መመለስ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ጥበበ፤ ይህንን ለማድረግም በራሳቸው ፍቃድ በዛሬው እለት አስር ቤቶችን ሰርተው ለአርሶ አደሮች ያስረከቡ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ጊዜያትም ክረምት ከመግባቱ በፊት በራሳቸው ወጪ እና በውጭ አለም የሚኖሩ ጓኞቻቸውን በማስተባበር ቤታቸው የወደሙባቸውን አርሶ አደሮች ሙሉ በሙሉ ወደ ቤታቸው ለመመለስ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

አካባቢው የጦር ቀጣና ሆኖ ከመክረሙ ጋር ተያይዞ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ አርሶ አደሮች ምንም አይነት ምርት እንዳላመረቱ ገልጸው፤ አርሶ አደሩ የሚቀጥለውን የምርት ዘመን ማምረት ይችል ዘንድ ለምርጥ ዘር እና የማዳበሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ በማበርከት ኢትዮጵያዊ ግዴታቸውን በመወጣት የበኩላቸውን እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። እነኝህ አርሶ አደሮች ለቀጣይ የምርት ዘመን ማምረት ይችሉ ዘንድ በውጭ ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአጤ ውሃ እና አካባቢው ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ወርቄ ቢምር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አማካኝነት ለአርሶ አደሮች እየተደረገ ያለውን ድጋፍ አድንቀው፤ በቀጣይ ባሉ ጊዜያት ሁሉንም አርሶ አደሮች ከዋሻ ወደ ቤታቸው ለመመለስ ድጋፋቸው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቁመዋል።

በአካባቢው የተደረገው ውጊያ አዝዕርት በሚመረትበት ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ባለፈው የምርት ዘመን አርሶ አደሮች አንድ እፍኝ እህል ወደ ቤታቸው እንዳላስገቡ ገልጸው፤በቀጣዩ የምርት ዘመን አርሶ አደሮች መሬታቸው ጦም እንዳያድር ለማድረግ መንግሥት እና ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ለአርሶ አደሩ የምርጥ ዘር እና የማዳበሪያ ግብዓት በማሟላት ሰብአዊ ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፈተና ውስጥ የተገኘውን የኢንቨስትመንት ውጤት ማስፋትና ማጠናከር ይገባል!

ሀገራችን በቅድመ ለውጥና ከለውጥ ማግስት አያሌ ፈተናዎች ተፈራርቀውባታል። በሀገር ውስጥ የነበረው የሰላም መደፍረስ ፣ ዓለም አቀፍ ክስተት የሆነው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ፣ የአሸባሪው ሕወሓት የጥቃት ወረራ ፣ የውጭ ኃይሎች የእጅ ጥምዘዛ ሙከራዎች እና ለአሸባሪው ቡድን ሲያደርጉት የነበረው ትብብር ትላልቅ ፈተናዎች ነበሩ። ሆኖም ግን ፈተናዎቿን በብቃትና በጥበብ ተቋቁማ በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ድሎችን ማስመዝገብ ችላለች፡፡

ታላቁን የህዳሴ ግድብ ከተደቀነበት ችግር አውጥቶ ኃይል እንዲያመነጭ ማድረግ፣ የተጋረጠብንን የሕልውና አደጋ በብቃት መወጣት መቻል፣ የዓለም ኢኮኖሚ በተንኮታኮተበት በኮሮና ወቅት እንኳን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ስትራቴጂን ተግባራዊ አድርጎ ኢኮኖሚው ጤናማ በሆነ መልኩ እንዲቀጥል ማድረግ ተችሏል።

ግዙፍ የልማት ስራዎችንና ፕሮጀክቶችን ጀምራ ማጠናቀቅ እንደምትችልም በተግባር አሳይታለች። ከዚሁ ጎን ለጎንም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ የተሰራው ስራ አንዱ የውጤት ማሳያ ነው። በተያዘውም የበጀት አመት እስካሁን ከሁለት ቢሊዮን ብር የዘለለ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ መቻሉን መረጃዎች ያመለክታሉ። ከሰሞኑም የተመረቀው ግዙፍ የብቅል ፋብሪካ የዚህ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ የእነዚህ ድምር ውጤትም የአገሩቱ ኢኮኖሚ በዓመቱ መጨረሻ በ6 ነጥብ6 በመቶ እድገት እንዲሚያስመዘግብ ተተንብዮዋል።

ለዚህም ውጤት አመላካች የሆኑ ማሳያዎችም መጥቀስ ይገባል። እስካሁን ሀገሪቱ በበጋ ወቅት ሰርታም ሆነ አይታ በማታውቀው መልኩ የበጋ ስንዴን ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ማምረት ተችሏል። አዳዲስ የቱሪዝም መስህብ የሆኑ ፕሮጀክቶች ተሰርተው ገንዘብ ማመንጨት ጀምረዋል። የወጪ ምርቶች ገቢ ማደግ ፣ እነዚህ ጥቂት የተጠቀሱና ሌሎች ልማቶች ድምር ውጤት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ማብሰሪያ ምልክቶች ናቸው። ስለዚህ የእስካሁኑን መልካም ጅምር ማስፋትና ኢንቨስትመንቱንም ማጠናከር ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ እስካሁን ከምታደርገው ባለሀብቶችን የመሳብና የመቀስቀስ እንቅስቃሴ በተሻለ መልኩ አስፈላጊውን ዝግጅትና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ጭምር ባለሀብቶችን እየጋበዘች ነው። እስካሁን ወደ ሀገራችን ገብተው በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች የተሰማሩ ባለሀብቶች አንዳንድ ችግሮች ቢያጋጥማቸውም እንኳን ችግሩን ተቋቁመውና ምቹ ሁኔታውን ተጠቅመው ደግሞ ውጤታማ ስራ እየሰሩ ናቸው። አሁን ደግሞ ከነበረው በተሻለ ሁኔታ የአገልግሎት አሰጣጡን የተገልጋዩን እንግልት እና ሌብነትን በሚቀንስ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው።

ኢትዮጵያ መጠነ ሰፊ በሆነ ሁኔታ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚፈልጉ ቁርጠኛ ባለሀብቶችን ለመቀበልና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዝግጁ መሆኗንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያ ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት በተሻለ ለኢንቨስትመንት በእጅጉ ምቹ ናት። የአየር ንብረቷ ፣ ያላት መሬት ፣ የሰው ጉልበት እና ሌሎችም ባለሀብቶችን የሚስቡ ናቸው። በመንግሥት ደረጃ መሬት በአነስተኛ ዋጋ በሊዝ ለባለሃብቶች የምታስተላልፍ ግንባር ቀደም ሃገርም ናት። ለፋብሪካዎች የሚያስፈልገውን የኤሌክትሪክ ኃይል በጣም በረከሰ ዋጋና በቀላሉ ታቀርባለች።

እንዲሁም ሰፊ የሰው ጉልበት የተማሩና በፍጥነት መማር የሚችሉ እንዲሁም በፋብሪካ ውስጥ መሥራት የሚችሉ ወጣቶች በስፋት ያሉባት ሀገር ናት። እነዚህ ሁሉ መልካም ዕድሎች ባለሀብቶችን የሚጋብዙ ናቸው። ምርቶቻቸውን በውጭ ሀገር በማቅረብና ሰፊ የህዝብ ቁጥር ባለበት ኢትዮጵያም በራሷ ሰፊ ገበያ በመሆኗም ባለሀብቶች በተለይ በአግሮ ኢንዱስትሪው፣ በግብርና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተሰማርተው ራሳቸውንም ኢትዮጵያንም መጥቀም እንደሚችሉ ይታመናል።

በመሆኑም በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥሪው ቀርቧል። ኢትዮጵያ ሰፊ አቅም ያላቸውንና በትክክለኛው መንገድ የሚሠሩ ባለሃብቶችን ለመቀበል ከምን ጊዜውም በላይ ፍላጎትና ዝግጁ ናት። ይሄንን ፍላጎቷን ለማሳካትም ባለፉት ሶስት ዓመታት ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ዘጠኝ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ሶስት አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መገንባት ችላለች።

በፈረንሳይ ባለሀብቶች ሰሞኑን የተመረቀው የብቅል ማምረቻ ፋብሪካም በፓርኮቹ ተጠቃሚ የሆነ አንዱ ግዙፍ ኩባንያ ነው። ሌሎች ግዙፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር የሆኑ የጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ፋብሪዎች የዚሁ እድል ተጠቃሚ ሆነው ራሳቸውንም ሀገራችንንም እየጠቀሙ ናቸው።

ይሄ በሀገሪቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ መኖሩንም ማሳያ ነው። እናም ሀገር በፈተና ውስጥ ሆና ያገኘችውን ዕድል በአግባቡ መጠቀም እና አዳዲስ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ወደ ሀገራችን እንዲመጣ ጠንካራ ሥራዎችን መስራት ይጠበቅብናል!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## “የወያኔን ዳግም ወረራ ለመቀልበስና ለመከላከል የውስጥ አንድነትን ማጠናከር፣ ሰላምና ደህንነትን መጠበቅ ቁልፍ ጉዳይ ነው”

- የአማራ ክልል የፀጥታው ምክር ቤት

“የወያኔን ዳግም ወረራ ለመቀልበስና ለመከላከል የውስጥ አንድነትን ማጠናከር፣ ሰላምና ደህንነትን መጠበቅ ቁልፍ ጉዳይ ነው” ሲል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጸጥታ ምክር ቤት የገለጸ ሲሆን፤ ምክር ቤቱ የአማራ ክልል ያለበትን የፀጥታ ሁኔታ በጥልቀት በመገምገም “ህዝባችን ዳግም ለወያኔ ወረራ ለጥቃት እንዳይዳረግ ቅድሚያ ሰጥቶ እንደወትሮው ሁሉ የፀጥታ መዋቅሩ፣ ደጀኑ ህዝብ የራሱን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ መሆን እንዳለበት” በማለትም አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፀጥታ ምክር ቤት በወቅታዊ የክልሉ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ ላይ ተወያይቶ ከትናንት በስቲያ ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፀጥታው ምክር ቤት ባደረገው ስብሰባ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ሁኔታ በዝርዝር ገምግሟል፡፡ የወያኔ ወራሪ ቡድን በየቀኑ የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ የትግራይን ህዝብ ለጦርነት እያነሳሳ በአማራ ክልል ላይ ዳግም ጦርነት አውጇል፡፡

ይህን አደገኛ ቅዠቱን ለመመከትና ለመቀልበስ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የክልሉ መንግሥት የፀጥታ ምክርቤት በአንክሮ ተወያይቶበታል፡፡ ጸጥታ ምክርቤቱ በየደረጃው ያለው የፀጥታ መዋቅር ዝግጁ መሆን እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

በሌላ በኩል በየደረጃው በተደረጉ ህዝባዊ ውይይቶች ላይ ጎልተው ከወጡ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል አንዱ የህግ ማስከበር ስራ መላላት ተጠቃሽ መሆኑን ጸጥታ ምክር ቤቱ በጥልቀት አንስቷል፡፡

በቅርብ ጊዜ ደግሞ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የአማራን የውስጥ አንድነት ለማዳከም፣ ህዝብ ከህዝብ በማጋጨትና በማጋደል ላይ ተሰማርተው ለጠላት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየሰሩ ያሉ የተደራጁና ያልተደራጁ ኃይሎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ተጨባጭ የፀጥታ ስጋት እየፈጠሩ መሆኑን በዝርዝር ተወያይቶበታል፡፡

እነዚህ ኃይሎች በእምነት፣ በፖለቲካ፣ በብሔር ህዝባችንን እየከፋፈሉ የአማራን የውስጥ አንድነት በማዳከም ለጥቃት ተጋላጭ እንዲሆን የሚያደርጉት ሙከራ በአጭር ካልተቋጨ በህዝባችንና በክልላችን ሰላምና ደህንነት ላይ ዘላቂ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

የህገ-ወጥ ንግድን በማስፋፋት ካለው ሀገራዊ የምርት እጥረት በተጨማሪ ሰው ሰራሽ የምርት እጥረት በመፍጠር የኑሮ ውድነት የሚያባብሱ፣ ምርትን ለጠላት በኮንትሮባንድ አሳልፈው የሚልኩ፣ የህዝብን ሃብት የሚዘርፉ፣ የዜጐችን ነጻ እንቅስቃሴ የሚገድቡ ድርጊቶች በየአካባቢው ያቆጠቆጡ መጥተው ለክልሉ የፀጥታ ስጋት መሆናቸውን ጸጥታ ምክርቤቱ ለይቷል፡፡ ከዚህም በላይ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች እየተስፋፋ የመጣው ህገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር የክልሉን ሰላምና ደህንነት ስጋት ውስጥ እየጣለ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም መሳሪያን ለመሞከር በሚል በሃዘንና በደስታ ላይ በግዴለሽነት በሚተኮስ ጥይት የንጹሀን ህይወት እየቀጨ እና የህዝባችን የፀጥታ ስጋትና የሃዘን ምንጭ እየሆነ መምጣቱን ጸጥታ ምክርቤቱ በአንክሮ ተመልክቷል፡፡

ህገ-ወጥነትና ስርዓት አልበኝነት ስር እየሰደደ በመምጣቱ ህገ-ወጥ ታጣቂዎች በሚያደርጉት ያልተገባ እንቅስቃሴ የክልሉን ልማቶች እያዳከመ፤ የዜጎችን ነጻ እንቅስቃሴ እየገደበ ፤ የኢንቨስትመንት እድሎችን እየዘጋ፣ የተፈጠረውን የስራ ዕድል እያጠፋ፣ ለቀጣይ ልማትም እንቅፋት በመሆንና በአጠቃላይ የአማራን ክልል ልማት በአደገኛ ሁኔታ እየተፈታተነ እንደሚገኝ አጽንኦት ሰጥቶ ተመልክቷል፡፡

እነዚህ ህገ-ወጥ ተግባራት በከተማም ሆነ በገጠር በአጭር ጊዜ ማረም ካልተቻለ የአማራ ክልል ልማት የሚያስቀጥል ሳይሆን የነበረውንም የሚያመክን የህገ-ወጥነትና የስርዓት አልበኝነት መናኸሪያ የሚያደርግ መሆኑን በመረዳት ለህዝብ ሰላምና ደህንነት ሲባል መልክ መያዝ እንዳለባቸው ታምኖበታል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቀለው የሚገኙ ወገኖቻችንም በአግባቡ ምግብ እንዲያገኙ አድርጎ ወደ ቀያቸው በጊዜ መመለስ ካልተቻለ የፀጥታና ሰብአዊ ቀውስ እንደሚያስከትል ፀጥታ ምክርቤቱ ተወያይቶበታል፡፡

ከዚህ አንጻር መንግሥት በየደረጃው ህግ የማስከበር ስራውን በጥብቅ በመፈፀም የህዝቡን ሰላምና ደህንነት ማስከበር አለበት በማለት ህዝቡ በተለያዩ መድረኮች ያነሳቸውን ጥያቄዎች መርምሮ ትክክለኛ ጥያቄ መሆኑን አስምሮበታል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጸጥታ ምክር ቤት የአማራ ክልል ያለበትን የፀጥታ ሁኔታ በጥልቀት በመገምገም የወያኔን ዳግም ወረራ ለመቀልበስና ለመከላከል የውስጥ አንድነትን ማጠናከር፣ ሰላምና ደህንነትን መጠበቅ ቁልፍ ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል። ህዝባችን ዳግም ለወያኔ ወረራ ለጥቃት እንዳይዳረግ ቅድሚያ ሰጥቶ እንደወትሮው ሁሉ የፀጥታ መዋቅሩ፣ ደጀኑ ህዝብ የራሱን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ መሆን እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

በመሆኑም በአንድ በኩል ከፌዴራል የጸጥታ መዋቅር ጋር በመቀናጀት ከወያኔ የሚሰነዘርብንን ጥቃት ለመከላከል በተጠንቀቅና በዝግጁነት መቆም፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣችን ለወያኔ ሴራ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩትን ህገ-ወጦችንና ስርዓት አልበኞችን በመቆጣጠር የክልላችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ግንባር ቀደም የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆኑ ወስኗል፡፡

ስለሆነም የክልሉ የጸጥታ ምክር ቤት በየደረጃው የጸጥታ ግብረ ሀይል አቋቁሞ ህገ-ወጥነትን ለመቆጣጠርና ህግን ለማስከበር ተገቢ ነው ያላቸውን ህጋዊ ርምጃ እንዲወስድ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

በመሆኑም የክልላችን ህዝብ፣ ወጣቶች ፣ የገጠርና የከተማ ኗሪዎች ሰላምና ደህንነታችንን ለመጠበቅ እና የውስጥ አንድነታችንን ለማጠናከር የፀጥታ መዋቅሩ በሚወስደው እርምጃ ሁሉ ተባባሪ እንድትሆኑ ጥሪያችን እናስተላልፋለን፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፀጥታ ምክር ቤት

ግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ.ም

ባህርዳር

ዜና

# አሸባሪው ሕወሓት በወረራ በያዛቸው አካባቢዎች በጦርነቱ ተሳትፎ ያልነበራቸውን 7 ሺህ የሚጠጉ ንፁሃንን መግደሉን ጥናቱ አመለከተ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በወረራ በያዛቸው አካባቢዎች በጦርነቱ ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበረቻቸውን 6 ሺህ 985 ንፁሃን ዜጎችን መግደሉን ጥናት አመለከተ ።

አሸባሪው እና ወራሪው የሕወሓት ቡድን ባካሄደው ወረራ በአማራ ክልል ያደረሰውን ጉዳት በተመለከተ በጥናት ውጤቱ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ እየተሰጠ ነው።

ጥናቱ አምስት ወራትን የወሰደ ሲሆን በአስር ዩኒቨርሲቲዎች እና በብሔራዊ ስታትስቲክስ ቢሮ ትብብር ሲደረግ የቆየ መሆኑ ተነግሯል።

ጥናቱ ቡድኑ በወረራ ይዟቸው ነፃ የወጡ የክልሉን ስምንት ዞኖች ያካተተ መሆኑ ነው የተገለጸው።

ቡድኑ በፈፀመው ወረራ ከ240 ሺህ በላይ ሰዎች የሰብዓዊ ጉዳት ሰለባ ሲሆኑ፤ 7ሺህ 460 ዜጎች ደግሞ በሃይል ታፍነው በመወሰዳቸው የት እንዳሉ አለመታወቁ በጥናቱ ተመላክቷል።

በጦርነቱ ሚና ሳይኖራቸው ከተገደሉት 6 ሺህ 985 ዜጎች ውስጥ 1 ሺህ 797ቱ በጅምላ ተጨፍጭፈው የተገደሉ መሆናቸው በሪፖርቱ ቀርቧል።

ቡድኑ ዘግናኝ ግድያዎችን ከመፈጸም በተጨማሪ እጅግ አስነዋሪ በሆኑ መንገዶች የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችንም ፈጽሟል ነው የተባለው።

የሽብር ቡድኑ ባደረሰው አስከፊ የሰብዓዊ ጉዳት የአስገድዶ መድፈር ሰለባ የሆኑት 1ሺህ 782 ዜጎች መሆናቸው ተነግሯል።



## አድናቆት የሚገባቸውን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለአፍሪካውያን ወጣቶች አርአያ መሆን የሚችል ስራዎች ማከናወን መቻላቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል።

በስራዎቻቸው የነበራቸው ጥንካሬ አይበገሬነትና ውጤት ለማምጣት በዘላቂነት ያከናወኗቸው ተግባራት ለክብር አብቅቷቸዋል፤ ወጣቶችም ከዚህ የክብር ሽልማት ብዙ ሊማሩ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሁለቱም ተሸላሚዎች በተሰማሩባቸው የግብርና ኢኮኖሚክስና የኢንጂነሪንግ ዘርፎች አፍሪካ ላይ መልካም ለውጥ ማሳየታቸውንም ገልጸዋል።

ዘርፎቹ ደግሞ ለአፍሪካውያን በተለይ በጣም አስፈላጊ ናቸው ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ የግብርናውን ዘርፍ ማየት ቢቻል የበርካታ አገራት የጀርባ አጥንት ነው። ኢትዮጵያም እራሷን በምግብ ለመቻልና ህልውናዋን ለማስጠበቅ በግብርናው ዘርፍ በተለይ በስንዴ ምርት ላይ ትልቅ ትኩረት እንዳላት ጠቁመዋል።

በዚህ ዘርፍ ውጤታማ ስራ በማከናወን እገዛ የሚያደርጉት የአፍሪካ ልማት ባንክ ግሩፕ ፕሬዚዳንት አኪንውሚ በጥረታቸው ምክንያት ላገኙት የክብር ሽልማት እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ በሙያቸው ያካበቱትን ልምድ ለሺዎች ማካፈል ቢችሉ መልካም ነው፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሚገኙ ወጣቶችም ዕውቀትና ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ አስፈላጊው መደላድል ይፈጠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌላኛውን የክብር ዶክትሬት ተሸላሚ ሳሊኒን እንኳን ደስ ያለዎት ብለው፤ በተለያዩ አገራት በኢንጂነሪንግ ዘርፍ በተለይም በመሰረተ ልማትና በግድብ ስራዎች ላይ ያሳዩትን ጥንካሬ አድንቀዋል።

ፔትሮ ሳሊኒ፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሲቪል ስራዎች ግንባታ ስኬታማነት ኃላፊነታቸውን በብቃት እየተወጡ መሆኑን ጠቁመው፤ በአፍሪካ አህጉርም የመሰረተ ልማት ዕድገት እንዲመዘገብ በርካታ ግንባታዎች ማከናወናቸውን አንስተዋል።

ጥራት ያላቸው የግንባታና መሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ለስራ ዕድል ፈጠራም ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አንስተው፤ ሳሊኒ በዚህ ረገድ ውጤታማ ስራ ማከናወኑን ገልጸዋል።

የሳሊኒ /ዊ ቢውልድ/ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ፔትሮ ሳሊኒ በበኩላቸው፤ ይህን ክብር እንደአገሬ በማያት ኢትዮጵያ በማግኘቴ ደስታ ይሰማኛል፤ አሁንም በተሰማራሁበት ሙያ ገንዘብን ሳይሆን የማህበረሰቡን ጥቅም ለማሳደግ በይበልጥ እሰራለሁ ብለዋል።

በተለያዩ አገራት ባከናወኗቸው የኮንስትራክሽንና የመጠጥ ውሃ እንዲሁም የመሰረተ ልማት ስራዎች በየቀኑ 100 ሚሊዮን ሰዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን የተናገሩት ሳሊኒ፤ አላማዬ ገንዘብ መሰብሰብ ሳይሆን ህብረተሰቡን ማገልገል ነው። ይህንንም ከልጅነቴ ጀምሮ በምመኘው የኢንጂነሪንግ ሙያዬ ማሳካት ችያለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ ግሩፕ ፕሬዚዳንት ዶክተር አኪንውሚ አዴሲና በበኩላቸው፤ በክብር ዶክትሬቱ ደስተኛ ነኝ፤ ከዚህ በኋላም ኢትዮጵያ ለምታከናውናቸው የልማት ስራዎች ድጋፍ ማድረጌንም እቀጥላለሁ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዕድገትና ተስፋ ከፊት ይታያል፤ በተለይ በመስኖ ስንዴ ላይ የሚከናወኑ ስራዎች ውጤታማ ናቸው። የአፍሪካ ልማት ባንክ ሁሌም ከኢትዮጵያ ጎን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በ30 ዓመት ልምዴ የአፍሪካን የድህነት ቅነሳ፣ የትምህርት መስፋፋት፣ የስራ ፈጠራና ሌሎችም ተግባራት ላይ ውጤታማ ስራ ለማከናወን በይበልጥ እጥራለሁ ብለዋል።

በክብር ዶክትሬት አሰጣጥ ስነስርዓቱ ላይ የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋና የተለያዩ ሚኒስትሮች እንዲሁም ቢሯቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉ የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች ተገኝተዋል።

## መንግሥት አፍራሽ ተልዕኮ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

13 ብሬል፣ 25 አረቤጅ፣ 25 ሳጥን የተለያዩ መጠን ያላቸው ጥይቶች፣አራት መትረየስ፣ አራት ስናይፐር መሳሪያዎች ተይዘዋል። በተጨማሪም በየቤተ እምነቶች የተቀበሩ ፈንጂዎች፣ የእጅ ቦንቦችና የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎች በሚስጥ ጥቆማ እየተሰበሰቡ መሆኑን ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ እየተከናወነ ባለው ህግ የማስከበር እርምጃ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ፣ በወለጋና በሌሎች አካባቢዎች ላይ በሚንቀሳቀሰው ሸኔ ላይ በተወሰደ ኦፕሬሽን በርካታ የቡድኑ አባላት ተደምስሰዋል፤ ተማርከዋል፤ በርካታ ትጥቆችና ተተኳሾችም በቁጥጥር ስር ውለዋል።

የመንግሥትን የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የማረጋገጥ ስራ በመቃወም ድምጻቸውን የሚያሰሙ አንዳንድ አካላት መኖራቸውን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ እነዚህ አካላት ወይ ወደ ሰላም መንገድ አሊያም ወደ ቡድኖቹ መግባትና ጎራቸውን መለየት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

በትግራይ ክልል ያልተገደበ የሰብአዊ እርዳታ እንዲቀርብ መንግሥት አሁንም ቁርጠኛ አቋም እንዳለውና በዚያ ልክም እየሰራ መሆኑን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ ባለፈው ሳምንት ብቻ 165 ከባድ ተሽከርካሪዎች መቐሌ መድረሳቸውን ተናግረዋል።

አሸባሪው ቡድን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር በወረራ ከያዛቸው አካባቢዎች እንደወጣ ቢያወራም አሁንም በአማራ ክልል በወረራ ከያዛቸው አዲአርቃይ፣ ጸለምት፣ አበርገሌ እና ሌሎች አካባቢዎች እንዲሁም ከአፋር ክልል ደግሞ ኮኖባ፣ በራህሌ፣ አብአላና መጋሌ ወረዳዎች እንዳልወጣ ገልጸዋል።

ከበባውን ለማስከፈት ሲባል የግድ ወደ ጦርነት ለመግባት እገደዳለው በሚል በአሸባሪው ሕወሓት የሚገለጸው የጦርነት ጉሰማና ፉከራ ዳግም የትግራይን ወጣቶች ለማስጨረስ ያለመ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑን ገልጸው፤ ይህን እኩይ እንቅስቃሴ የትግራይ ሕዝብ መታገል እንዳለበት አሳስበዋል።

መንግሥት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የኑሮ ውድነትንና፣ የስራ አጥነት ችግሮችን ለመቅረፍ በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት እየተስተዋለ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቅረፍ መንግሥት የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ ነድፎ እየሰራ መሆኑንም ሚኒስትሩ በመግለጫው አስታውቀዋል።

ዋናው የኑሮ ውድነት ችግር ከምርት አቅርቦት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ስንዴ፣ ዘይት፣ አልሚ ምግብና ስኳር የመሳሰሉ ምግብ ነክ ፍጆታዎች በአጭር ጊዜ ለመቅረፍ በፍራንኮ ቫሉታ አሰራር የራሳቸውን የውጭ ምንዛሬ ተጠቅመው እንዲያስገቡ ፍቃድ ተሰጥቷል። በተጨማሪም በግዥ ስርዓቱ ላይ ያሉ መስተጓጉሎችን ለመቅረፍ እየተሰራ ስለመሆኑ ለገሰ ቱሉ (ዶክተር) በመግለጫቸው አመላክተዋል።

## "ሀገራችን ኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደሚያገኙ ተናግሯል፡፡

እንደ ድምፃዊ አቡሽ ንግግር፤ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ስፍራዎች የሚነሱ ጸቦች ለኢትዮጵያ ትልቅነት የማይመጥኑ፣ ኢትዮጵያን የማይመስሉና አሳፋሪ በመሆናቸው ሁሉም ሰው ቆም ብሎ በማሰብ የሚወዳትን ሀገሩን ሰላሟን የመጠበቅ ስራን ሊከውን ይገባዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በየቀኑ ደስ የማይሉ ነገሮችን መስማትና ማየት እየተለመደ መምጣቱን የጠቆመው ድምፃዊ አቡሽ፤ አብዛኛው ህዝብ የሀይማኖት ተከታይ በሆነባት ሀገር በግጭት ውስጥ መሳተፍ የእምነቶቹን ትዕዛዝ ያለማክበር ጭምር እንደሆነም ተናግሯል፡፡

በክፉ ተነሳስቶ ቂም በቀል ማትረፍ ለማንም አይጠቅምም፤ በያዝነው የመገፋፋት መንገድ ከሄድን ማንም ተጠቃሚ አይሆንም ያለው ድምጻዊ አቡሽ፤ ከእንደዚህ አይነት አፍራሽ ድርጊቶች ራሳችንን በማራቅ ኢትዮጵያን ለቀጣይ ትውልድ ከእነ ክብሯ ማስተላለፍ ያስፈልጋል ሲልም ገልጿል፡፡

ድምፃዊ አቡሽ ኢትዮጵያን አላወቅናትም እንጂ ብናውቃትና ብትገባን ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የምትተርፍ ሀገር ናትና ባልጠበበችን ሀገር አንገፋፋ፤ በፍቅር በአንድነት እንኑር የሚል መልእክቱንም አስተላልፏል፡፡

ከትናንት መማር እንደሚያስፈልግ የገለፀው ድምጻዊ አቡሽ፤ ከግጭት ማንም ስለማያተርፍ በመረጋጋትና በአንድነት በመኖር ለልጆቻችን ምቹ የሆነች ኢትዮጵያን ልናስረክብ ይገባናል ሲልም ገልጿል፡፡

እዚህም እዚያ የሚከሰቱ የሰላም መደፍረሶችን ለማስቀረትም ታዋቂና ፖለቲከኛ ሰዎች ህዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ ስለሚናገሩት ነገር ሊጠነቀቁ እንደሚገባ የገለጸው ድምፃዊ አቡሽ፤ ወደ መድረክ ወጥተን የምንናገረው ነገር ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ዝነኛ ሰዎች አኗኗራቸውና ንግግራቸው ያንን ያገናዘበ መሆን ይገባዋል ሲልም ገልጿል፡፡

ሁሉም በሚወዳትና በሚመኛት ሀገር አንገፋፋ፤ በፍቅር በአንድነት እንኑር የሚል መልእክቱንም አስተላልፏል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የመቤዠት ፖለቲካ ...!?

ሃገራችን የምትገኝበትን እጅግ ውጥንቅጥ ፣ ውስብስብና ጥልፍልፍ ነባራዊ ሁኔታን መልሼ መላልሼ ባንሰላሰልሁ ፤ ታጥቦ ጭቃ ስለሆነው ሁለነገራችን በቆዘምሁ ፤ መውጫ መንገዳችን ከእርዮተ አለምና ከሥርዓት በላይ መሆኑን በታዘብሁ ፤ እንደ ዜጋ ከዚህ ቀለበት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሰብሮ ለመውጣት የጋራ ጉልበት እየከዳን እንደሆነ ሲሰማኝ ፤ ለችግሮቻችን መፍትሔ ይሆናሉ ብለን ያሰብናቸው ነገሮች ሁሉ ባልተጠበቀና ባልተገመተ ሁኔታ አባባሽና አቀጣጣይ ቤንዚን ሆነው ሳገኛቸው ፤ ከርቀት የሚታየኝ ተስፋ ስደርስበት የሀሩር ሚራዥ እየሆነ ግራ ሲገባኝ ፤ የሔድንባቸውም ሆኑ የመጣንባቸው መንገዶች ከዋሻው አውጥተው ብርሀን ማሳየት ሲሳናቸው ፤ ያልሔድንባቸውንም ሆነ ያልመጣንባቸው መንገዶች አሳሽና ተቅበዝባዥ ሁኜ አረፍሁት።

ጥንታዊውን የሀገራችንን ታሪክ አቆይተነው ፤ ከዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ወዲህ ማለትም አፄ ቴዎድሮስ ከነገሱበት ዘመን ወዲህ እስከ ዛሬ ያለውን መለስ ብለን ገለጥ ገለጥ ብናደርግ እንኳ፤ ለነጻነታችን ፣ ለሉዓላዊነታችን ፣ ለአንድነታችን ፣ ለግዛት አንድነታችን፣ ለእኩልነታችን ፣ ለፍትሕ ፣ ለዴሞክራሲ ፣ ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታችን ፣ ለሰላም ፣ ለፍቅር ፣ ለይቅር ባይነት ፣ ለመደማመጥ ፣ ለመነጋገር ፣ ለመቀባበል ፣ ከድህነትና ከኋላቀርነት ፣ ከመሀይምነትና ከድንቁርና፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል ፣ ከሴራና ከደባ ፣ ከአቅላይነት ለመላቀቅ ፤ ለእድገት ፣ ለብልጽግና ፣ ወዘተረፈ ጎልቆ መሳፍርት የሌለው ደም ብናፈስ ፣ አጥንት ብንከሰክስ፣ አካል ብናጎድል ፣ ሺህዎችን ብናጉር ፣ ብናሰቃይና ብናሳድድ ፤ ነጭ ላብ በጀርባችን ብናቆረቁር ፣ ከዚህም ከዚያም የተቀራረመ እውቀት ብናፈስ ፣ ጉልበት ብናባክንም ከሁለንተናዊ ቀውስ አዙሪት በማያዳግም ሁኔታ ሰብረን መውጣት አልቻልንም ። ነገረ ሥራችን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንደሆነ ቀጥሏል ።

በአድዋ ፣ በማይጨው ፣ በካራማራ ፣ በከረን ፣ በባድመ ፣ ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ደግሞ ከአሸባሪው ሕወሓትና ከቡችሎቹ ጋር ፣ ወዘተረፈ በመቶ ሺህዎች ደማችንን አፍስሰን አጥንታችንን ከስክሰን ፤ በርካታ ቢሊዮኖችን ገፍግፈን ዛሬም ሃገረ መንግሥቱን በሁለት እግሩ ማቆም ላይ እየተውተረተርንና እየተፍገመገምን እንገኛለን ። አንዳንድ ጊዜ አንድ እርምጃ ወደፊት ሁለት እርምጃ ወደኋላ እየሄድን፤ ሌላ ጊዜ ባለንበት እየረገጥን እንገኛለን ። የፓርቲ ፖለቲካ ታሪካችን ከግማሽ ክፍለ ዘመን ቢሻገርም ዛሬም አድሮ ቃሪያዎች ነን ። ለትግል የፖለቲካ ፓርቲ ያስመሠረቱን ጥያቄዎች ዛሬም በቅጡ አልተመለሱም ። ቀይ ሽብር ፣ ነጭ ሽብር ብለን አንድ ወርቃማ ትውልድ የጨረስንበት ሕዝባዊ መንግሥት ከእነ ውስንነቱ ገና የሁለት ዓመት ጨቅላ ስለሆነ ወፌ ቆመች ! ወፌ ቆመች ! እያልነው እንገኛለን ።

የመጣ የሄደው አገዛዝ ተቋማትን በአምሳያው ጠፍጥፎ ለመሥራት ሲያፈርስ ሲሠራቸው በሁለት እግራቸው መቆም ተስኗቸው እየተንገዳገዱ ዛሬ ላይ ደርሰዋል። በዚህ የተነሳ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ፤ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን መመለስ፤ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ፤ ብሉሽ አሠራርን ማስወገድ ፤ የገነገነ ሙስናን ከስሩ መንግሎ መጣል ፤ ጠንካራ ነጻና ገለልተኛ ሚዲያ መገንባት አልቻልንም ። ያን ሁሉ መስዋዕትነት ከፍለን ዛሬም የምንመኘውንና የምንፈልገውን ሥርዓት ማምጣት አልቻልንም ።

በነገራችን ላይ ትላንትም ሆነ ዛሬ እያለፍንባቸው ላሉ ውድቀቶችና ቀውሶች እንደ ሕዝብም እንደ መንግሥትም ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን ። የሚገባንና ይበላቸው የሚያሰኝ አገዛዝ እንዲፈራረቅብን የሆነው ከዚህ ለተሻለ ሥርዓት ዝግጁ ስላልሆን ነው። በስንትና ስንት መስዋዕትነት ያመጣነውን ለውጥ ለሃገርና ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ስላላበጀነው ፣ ስላልጠበቅነውና ስላልተከላከልነው በምንም ሊተመን የማይችል ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል ። የ66ቱን እና የ83ቱን ይቅርና አሁን የምንገኝበትን ለውጥ እየተከላከልነውና እየጠበቅነው አይደለም ። ለዚህ ነው ከዚህ አዙሪት በማያዳግም ሁኔታ ሰብሮ መውጣትና አዲስ ምዕራፍ መከፈት ግድ የሚለን ።

> **ጎሰኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ግጭትን፣ ሴራን ፣ ወዘተረፈ በቤቴ ፣ በእምነት ተቋሜ ፣ በፖለቲካ ፓርቲዬ፣ በትምህርት ቤቴ ፣ በመደበኛና ማኅበራዊ ሚዲያዬ ፣ ወዘተረፈ አልተባበርም ፣ አላስተናግድም ነው ሞቱ። እነዚህን ጣኦታትን ከአዕምሮ ጓዳችን አውጥተን መጣል ፣ ማንከባለልና መስበር ነው ሞቱ ። ይሄን ስናደርግ የዚህ ጊዜ ስህተቶቻችንን አርመን ፤ ጥፋቶቻችን አስተካከልን ፤ እድፍና ጭቅቅታችንን አጸዳን ተቤዠን ማለት ነው። ዳግም እንዳንመለስባቸው ተቆራረጥን ማለት ነው ። እንደ ንስር ታደስን ፣ በከፍታ በረርን ማለት ነው**

እንደ ልዑል እግዚአብሔር አንድያ ልጆቻቸውን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አጋፔያዊ ለሆነ ፍጹም የሃገርና የሕዝብ ፍቅር አባቶችና እናቶች አሳልፈው በሰጡን አንድያዎቻቸው መስዋዕትነትና ከፍ ብሎ እንደተመለከተው እደግመዋለሁ ፤ ከጦርነት፣ ከግጭት ፣ ከልዩነት፣ ከጥላቻ ፣ ከቂም ፣ ከበቀል፣ ከጎሰኝነት ፣ ከሌብነት ፣ ከስግብግብነት ፣ ከአልጠግብ ባይነት ፣ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል ባይነት ፣ ከአቅላይነት ፣ ከሴረኛነት፣ ከድህነት ፣ ከኋላቀርነት ፣ ከረሀብ ፣ ከእርዛት፣ ከቁሞ ቀርነትን አባዜ ፣ ከሐሰተኛ ትርክት ለፋፊነት ፣ ከተጠቂነት አባዜና ከቸነፈር ሊቤዡን ካልቻሉ፤ ኃጢያታችንና በደላችን ከተከፈለልን ዋጋ በልጦ ይሆን ብዬ ብቸገር ሊመጣጠን ይችላል ያልሁትን ከዚህ ቀደም ያልተከፈለ ዋጋና መስዋዕትነት ለጣኦቶቻችን ይገዬ መጥቻለሁ። ዋጋውንም ሆነ መስዋዕትነቱን ሁላችንም ለምናመልካቸው ጣኦቶቻችን አንድ በአንድ የምንከፍለው ነው ። እሱም መሞት ነው ። አዎ መሞት ! አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደግሞ ደጋግሞ መሞት ነው የጣኦታቱ ምስ። በቤተሰብ መሞት ፣ በትምህርት ቤት መሞት፣ በአብያተ ክርስቲያናት መሞት፣ በመስጅዶች መሞት ፣ በዋርካው ጥላ መሞት፣ በመሥሪያ ቤት መሞት ፣ በፖለቲካ ፓርቲ መሞት ፣ ወዘተረፈ በመሞት ለጣኦቶታቻችን ምስ መሆን።

አዎ! ጸረ ሕዝብና ሃገር ለሆኑ ጣኦታት ያለመተባበርና ያለመገዛት ሞት ነው ምሱና መፍትሔው። ከልዑል እግዚአብሔር ፣ ከነብዩ መሐመድ ፣ ከዋቄ ፈና እና ከሌሎች አማልክት በላይ ለምናመልካቸው ጣኦታት መሞት። ካስፈለገም መሰቀል። ሞቱ አካላዊ ሞት አይደለም። ለጣኦታቱ አልገብርም ፤ መስዋዕት አላቀርብምና አልተባበርም የማለት የአስተሳሰብና የአመለካከት ሞት እንጂ። ለመሆኑ እነዚህ ጣኦቶቻችን እነማን ናቸው ብላችሁ ግራ እንዳትጋቡ ፤ ለፍለጋም ሩቅ እንዳትሔዱ ፤ ደምና ሕይወት እየገበርን ያደለብናቸው ሰርክ በእብሪትና በትዕቢት በእያንዳንዳችን አዕምሮ ጓዳ የሚጎማለሉ ጣኦታት ናቸው ። ጎሰኝነት ፣ ጥላቻ ፣ ልዩነት ፣ ቂም በቀል ፣ ሌብነት ፣ የፈጠራ ትርክት ፣ ደባና ሴራ ፣ ወዘተረፈ እና ከፍ ብሎ ከአንድም ሁለት ጊዜ ለመዘርዘር የሞከርኋቸው ናቸው ጣኦታቱ ። አዎ ለእነዚህና መሰል ጣኦታት አምልኮ መሰዊያ ላይ ላለመገኘት መወሰንና መቁረጥ ነው ሞቱ ።

ጎሰኝነትን ፣ ጥላቻን ፣ ግጭትን ፣ ሴራን ፣ ወዘተረፈ በቤቴ፣ በእምነት ተቋሜ ፣ በፖለቲካ ፓርቲዬ ፣ በትምህርት ቤቴ ፣ በመደበኛና ማኅበራዊ ሚዲያዬ ፣ ወዘተረፈ አልተባበርም ፣ አላስተናግድም ነው ሞቱ ። እነዚህን ጣኦታትን ከአዕምሮ ጓዳችን አውጥተን መጣል፣ ማንከባለልና መስበር ነው ሞቱ ። ይሄን ስናደርግ የዚህ ጊዜ ስህተቶቻችንን አርመን ፤ ጥፋቶቻችን አስተካከልን፤ እድፍና ጭቅቅታችንን አጸዳን ተቤዠን ማለት ነው። ዳግም እንዳንመለስባቸው ተቆራረጥን ማለት ነው ። እንደ ንስር ታደስን ፣ በከፍታ በረርን ማለት ነው ።

ጀግኖቻችን ለዘመናት ሞተውልን ካልተቤዡን፤ የቀረን ነገር በኃጢያታችን የተነጠቅነውን ፣ አሳልፈን የሰጠነውንና ያጣናውን ምርኮ ማስመለስ የምንችለው ሁላችንም ሞተን ሃገራችንና ሕዝባችን መቤዥና መታደግ ስንችል ብቻ ነው ። ለዚህ የሚበጀው ደግሞ የመቤዠት ፖለቲካ ነው ። በመተላለፋችን ፣ በኃጢያታችንና በበደላችን ለዘመናት የተነጠቅነውንና ያጣነውን ምርኳችንን የሚያስመልስልን ፤ ስህተቶቻችንን የሚያርምልን ፣ የሚያስተካክልልንና እድፋችን የሚያነጻልን ዋጋ ማለትም መሞት ብቻ ነው።

የሶሻሊስትና የልማታዊ/የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካ አሳራችንን አበዛው እንጂ መፍትሔ አላመጣም። መደመር/...ሪዝምን ለመገምገም ጊዜው ገና ቢሆንም የመቤዠት ፖለቲካ አይነት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። “መደመሪዝም” በአንድም በሌላ በኩል ስህተትንና ጥፋትን የማረም ፤ እንደ ሃገር ፣ ሕዝብና ኢትዮጵያዊ ያጣነውን ወረት የማስመለስ ግብን ያነገበ ስለሆነ ለመቤዤት ፖለቲካ ይቀርብብኛል ። ምንም እንኳ ብልጽግና ራሱ ደፍሮና አፉን ሞልቶ ሃገር በቀል ርዕዮተ ዓለም ነው ባይለንም እኔ ግን በዚህ ማንጸሪያ ነው የምመለከተው ። “መደመሪዝም” እንደ አዲስ እይታ ብቻ ሳይሆን እንደ ርዕዮተ ዓለም ተወስዶ ሊጠናና ሊተነተን ይገባል የሚል እምነት አለኝ ።

ሃገራችንንና ሕዝባችን ለማዳን የቀረን ብቸኛ ነገር ቤዛ መሆን ነው ። በብዙ እዳ የተያዘችውንና የተወሰደችውን ሃገራችንና ሕዝባችን ሁላችንም ዋጋ ፣ ካሳና ለውጥ ከፍለን ማስመለስ የቀረን ብቸኛ አማራጭ ነው። ኢየሱስ ለሚያምኑበት ሁሉ በሞቱ ቤዛ ሆኖ ከዘላለማዊ ሞት እንዳዳናቸው ፤ በሞታችን ቤዛ ሆነን ሃገራችንን ከሞት ማዳን አለበን ። ቤዛ የምንሆነው በሮማውያን መስቀል በቀራኒዮ ተሰቅለን አይደለም። የምንሞተው ሃገራችንና ሕዝባችን ለዚህ ህልቆ መሳፍርት መከራና አሳር ለዳረጉ እኩይ ተግባራት ከዚህ በኋላ ላለመተባበር በመወሰንና በመማማል ነው ።

የተፈጸሙ ስህተቶችንና እንደ ጎን ውጋት አላላውስ ብለው ቀስፈው የያዙንን ችግሮች ለጊዜያዊ ፖለቲካ ጥቅም ከማዋል ይልቅ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለማረምና ለማስተካከል መረባረብና መጣር አለብን ። የሁሉም ዜጎችና ተቋማት ግብም በዚህ የተቃኘ ሊሆን ይገባል። የፖለቲካ ፕሮግራማችን ፣የልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎቻችን ፣ ሥርዓተ ትምህርታችን ፣ የታሪክ ትምህርታችን፣ የዐውደ ምሕረት ስብከታችን ፣ ወዘተረፈ የቀደሙ ስህቶቻችን ለማረም የሚተጉ እንጂ በጥፋት ላይ ጥፋት ፣ በችግር ላይ ችግር ፣ በቀውስ ላይ ሌላ ቀውስ የሚለፍፉና የሚጋብዙ መሆን የለባቸውም።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !**

**አሜን።**

ማህበራዊ

## የሕይወት ገጽታ

# ያልተዘመረላት ደማቅ ፀሐይ

**አሥመረት ብሥራት**



ፎቶ ፡ ገበቡ ገብሬ

ከሠላሣ ዓመታት በላይ "ሥራዬ ቋሚ ምስክር ይሁነኝ። እኔ በአደባባይ ወጥቼ ይህን ሠራሁ ብዬ አልናገርም።" በማለት ሥራ ሥራቸውን ብቻ ሲሠሩ የቆዩ፤ በርካታ ሕፃናትን አሳድገው ለወግ ማዕረግ ያበቁ፤ አንድም ቀን "እኔ ይሄን ሠራሁ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለፈቀደ እኔን መጠቀሚያ አደረገኝ።" በማለት ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑትን አንድ ታላቅ ሰው እንተዋወቅ።

ወይዘሮ ፀሐይ ሮሽሊ ይባላሉ። አጠር ያለ ቁመታቸው ላይ የለበሱት የሃገር ልብስ ፍክት አድርጋቸዋል። ፈገግታቸውና አስተያየታቸው ፍፁም እናታዊ ነው። ንግግራቸው የተቆጠበ ሲሆን፤ በተረጋጋ አንደበት እንዲህ ተጨዋውተውናል መልካም ንባብ።

ለመቶ አለቃ ድልነሳው አላምረው እና ለወይዘሮ አበባ ፍቅረማሪያም የመጀመሪያ ልጅ የሆነችው ፀሐይ በ1948 ዓ.ም በአዲስ አበባ አሮጌ አውሮፕላን ማረፊያ አከባቢ ይችን ዓለም ተቀላቀለች። ታናናሾቿ ከሆኑት እህት ወንድሞቿ ጋር እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ልጅ ቤተሰቦቿን እያገለገለች አደገች። ቤታቸው ላሞች ዶሮዎች በርካታ የቤት እንስሳት የሚገኙበት እንደነበር ታስታውሳለች።

ትንሿ ፀሐይ አንድ ቀን በቤታቸው አቅራቢያ በሚገኝ አንድ ወንዝ አካባቢ እየተጫወተች የውጭ ሃገር ዜጎች ተመለከተች። ቀደም ሲል ከእነሱ የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸውን ሰዎች ተመልክታ ስለማታውቅ ተገርማለች። ምን እንደሚመስሉ በቅርበት ለመመልከት ጠጋ ትላለች። የነጮቹ ልጆቹ ይጫወታሉ፤ እናታቸው ቁጭ ብላ ልጆቿን ትመለከታለች። ፀሐይ ፈረንጆች እንቁላል ይወዳሉ የሚል ነገር ትሰማ ስለነበር በሩጫ ወደ ቤቷ ተመልሳ እንቁላል አምጥታ ሰጠቻቸው። ቋንቋ በሌለበት ዝም ብለው ሲተያዩ ከቆዩ በኋላ በእጅ ምልክት ወደ ቤቷ ጋበዘቻቸው። እነሱም ተከትለዋት ወደ'ነፀሐይ ቤት ሲገቡ የፀሐይ እናት ላም እያለበች ያገኟታል። የፀሐይ እናትም ከምታልበው ወተት ቀድታ ሳትሰስት ለእነዚህ ነጮች ትሰጥና በምስጋና ይሰነባበታሉ።

በቀጣዩ ቀን በፌስታል የተሞሉ ምግቦች፤ አልባሳት፤ መጫወቻ ብቻ ምኑ ቅጡ ለልጆች ያስደስታል የተባለውን ሁሉ ይዘው መጥተው ያለ አንዳች ንግግር ሲተያዩ ቆይተው ፀሐይን ይዘዋት ሜክሲኮ፣ ትንባሆ ሞኖፖል አካባቢ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ሄዱ። ፀሐይ በሕይወቷ አይታ የማታወቀውን አይነት ቤት ስታይ በጣም ተገረመች። ከነጮቹ አራት ልጆች ጋር በመሆን ስትጫወት ከቆየች በኋላ ወደ ቤቷ ትመለሳለች።

እንዲህ እንዲህ እያለ ያለ ምንም ንግግር የተግባቡት እነዚህ የሁለት ዓለም ሰዎች ዝምድናቸው እንደመጥበቅ ኣለ። በመሐል የፋሲካ በዓል ስለነበር እነፀሐይ ቤት እንዲመጡ ነጮቹ ግብዣ ተደረገላቸው። በወቅቱ ጠረጴዛውንም ከነጮቹ ቤት በመበደር ቤት ያፈራውን ዶሮም፤ ጥብስም፤ ዱለትም፤ ከየዓይነቱ ለበዓል የተዘጋጀው ምግብ ለእነዚህ ሰዎች ቀረበ። በፍፁም ኢትዮጵያዊ መስተንግዶ ሲደሰቱ ውለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ከዛ በኋላ በዚህ ቤተሰብ ፍቅር የወደቀችው ነጯ ሴት አስተርጓሚ የሚሆን ሰው እቤታቸው ይዛ መጥታ ፀሐይ ከእነሱ ጋር እንድትኖር ተጠየቀ፤ ከዛም የፀሐይ ወላጆች ተማክረው ልጃቸው ወደ ነጮቹ ቤት ሄዳ እንድታድግ ተወሰነ። የሶስተኛ ክፍል ተማሪ የነበረችው ፀሐይ ከነጮቹ ልጆች ጋር በመሆን ጀርመን ትምህርት ቤት አንደኛ ክፍል ተመልሳ እንድትገባ ተደረገ።

በዚህ መካከል ፀሐይ ወላጆቿንም እየጠየቀች ስትኖር የፀሐይ አባት በጠና ታመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ብዙም ሳይቆይ የፀሐይ እናት ባላቸውን ተከትለው ልጆቻቸውን ያለ አሳዳጊ በትነው አረፉ። ያኔ በአቅራቢያቸው የነበሩ የእነፀሐይ አጎትና አክስት ልጆቹን ተከፋፍለው ለማሳደግ ተስማሙ። የእነ ፀሐይን ኀዘን ኀዘናቸው አድርገው የሰነበቱት ነጮች ግን እነዚህ ሕፃናት ተለያይተው ማደግ የለባቸውም፤ መፍትሔ እንፈልጋለን ብለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ቤታቸው እንደደረሱ ልጆቻቸውን ሰብስበው የፀሐይን ወንድም እህቶች ይዘን ልንመጣ ነው ብለው ሲያማክሯቸው በደስታ ተስማምተው ልጆቹ ወደ ነጮቹ ቤት ሄደው እዛ እየኖሩ መማር ጀመሩ። የራሳቸውን አራት ልጆች ለማሳደግ የመጡት፤ ስድስት ልጆች ተጨምረው አንድ ላይ አስር ልጆችን ያሳድጉ ጀመር።

አሳዳጊ አባቷ ዴቪድ ሮሽሊ፤ አሳዳጊ እናቷ ሜሪ ሊውስ ሮሽሊ የራሳቸው አራት ልጆች ያሏቸውና ከተጨማሪዎቹ የፀሐይ እህት ወንድሞች ጋር አስር ልጆችን ለማሳደግ ኑሮው ከበድ ይል ስለነበር በሰበታ አካባቢ ዶሮ የማርባት ሥራ ጀመሩ። የፀሐይ አሳዳጊዎች ዶሮውን አርደው ለሱፐር ማርኬቶች የማከፋፈል ሥራንም ይሠሩ ነበር።

በዚህ መካከል የንጉሡ ዘመን አብቅቶ የደርግን ወደ ስልጣን መምጣት ተከተሎ የእነ ፀሐይ አሳዳጊዎች ከሃገር መውጣት ግድ ይሆንባቸዋል። ያኔ እናሳድጋቸው ብለው የወሰዷቸውን ልጆች ጥለው የመሄዱ ነገር ጭንቅ ሆኖባቸው ወደ ኤምባሲ በመሄድ ልጆቹን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያማክራሉ። ኤምባሲው በማደጎ መውሰድ እንዲችሉ ደብዳቤ ለመፃፍ ተስማምተው አስሩንም ልጆች ይዘው በጅቡቲ በኩል ከሃገር ወጡ።

የወለዷቸውን ልጆች አባታቸው ይዘው ወደ ሲዊዘርላንድ ቢሄዱም አሳዳጊ እናታቸው ግን ወረቀታቸው ተስተካክሎ ልጆቹን ይዛ ወደ ሃገሯ እስከትሄድ ድረስ ለአራት ወራት የምታሳድጋቸውን ልጆች ይዛ ጅቡቲ ከቆየች በኋላ ልጆቿን ይዛ ወደ ትውልድ ሃገሯ ስዊዘርላንድ ገባች።

ገና ልጆች ይዛ የመምጣቷን ዜና የሰሙት ዘመድ ጎረቤቶቿ ለተጨማሪዎቹ ልጆች የሚሆኑ አልባሳትና የምግብ ቁሳቁሶች ከማዘጋጀታቸውም ባሻገር የአሳዳጊ እናቷ ወንድም ቤት በመስጠት እንዲመቻቸው ለማድረግ ተረባረቡ።

ፀሐይ ገና ፈረንጅ ሃገር እንደሄደች በወቅቱ የምታውቀው ትልቅ ሕንፃ የንግድ ባንክ የነበረ ሲሆን እዛ ሃገር ሁሉም በሰፊ ቤት፣ በትልልቅ ሕንፃ ውስጥ የሚኖሩ ይመስላት እንደነበር ትናገራለች። ነገር ግን ጠበብ ባለ ቦታ እየኖሩ ባላቸው ትንሽ መሬት አስፈላጊ አትክልቶችን በመትከል በደስታ የሚኖሩት የስዊዞቹ ቤተሰቦቿን ኑሮ ስታይ በጣም እንደተገረመች ትናገራለች።

ስዊዘርላንድ ስትደርስ የአስራ ዘጠኝ አመት ወጣት የነበረችው ፀሐይ እህት ወንድሞቿ ወደ ትምህርት ቤት ቢሄዱም እሷ አሳዳጊ እናቷ ላይ የወደቀው ልጅ የማሳደግ ኃላፊነትን ለመርዳት ቤት ትቆያለች። ኢትዮጵያ እያሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበሩት አሳዳጊ አባቷ ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ በተማሩበት ዘርፍ ሥራ ማግኘት ባለመቻላቸው የተገኘውን ሥራ በመሥራት ሰፊውን ቤተሰብ ለማስተዳደር ደፋ ቀና ይሉ ጀመር። በዚህም ሰዎች ባላቸው ይረዷቸው ጀመር። ፀሐይም አሳዳጊዎቿን ለመርዳት የሚያስችላትን የፋብሪካ ሥራ መሥራት በመጀመር በመረዳዳትና በፍቅር ኑሮን መግፋት ጀመሩ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ፀሐይ ቤት ተከራይታ በመውጣት የራሷን ኑሮ መኖር ጀመረች። በወጣትነት ጊዜዋ መሥራትን፤ ገንዘብ ማግኘትን፤ ዓለምን መዞርን፤ ሕልሟ ያደረገችው ይች ወጣት ቀን በፋብሪካ ስትሠራ ውላ ማታ ደግሞ ቢሮ በማፅዳት ሥራ ላይ ተሠማርታ ገንዘብ ማጠራቀም ጀመረች። የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሊያልፍ የቀረቡ ምግቦች በርካሽ ስለሚሸጡ እነሱን በመግዛት እየተመገበች ገንዘብ ላለማባከን እየተጠነቀቀች የምትኖረው ፀሐይ አንድ ቀን ሕይወቷን የቀየረውን ዜና በቴሌቪዥን ትመለከታለች።

ከሠላሳ አምስት ዓመታት በፊት ፀሐይ ወደ ስዊዘርላንድ ከሄደች ከአስራ ሦሥት ዓመታት በኋላ ሃገሯን አስታወሰች፤ ሀብታም መሆን፣ መኪና መግዛት፣ ቤት መግዛት ሕልሟ የነበረው ይች ልጅ ሃገሯ በረሃብ እየተጎዳች ወገኖቿ እንደቅጠል እየረገፉ እንደሆነ የሚያሳይ ዜና ነበር የተመለከተችው። ሃገሯን ረስታ

> "ሃገሯን ረስታ የቆየችው ወጣት ቀኑን ሙሉ የሰማችው ነገር ሲከነክናት ዋለ። ሲከነከናት የዋለውን ዜና ዳግም በማታው ስርጭት ተመለከተች። ያ ሀብታም የመሆን ሕልሟ፤ ያ ዓለምን የመዞር ታላቅ ሰው የመሆን ሀሳቧ ሁሉ ተቀይሮ "እንዴት ነው ለወገኔ የምደርሰው?" በሚል ሀሳብ ተተካ። ከገንዘብ በላይ የሰው ልጆችን ነፍስ ለማትረፍ የሚያስችል በጎ ተግባር ለመሥራት ቆርጣ ተነሳች።"

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

የቆየችው ወጣት ቀኑን ሙሉ የሰማችው ነገር ሲከነክናት ዋለ። ሲከነክናት የዋለውን ዜና ዳግም በማታው ስርጭት ተመለከተች። ያ ሀብታም የመሆን ሕልሟ፣ ያ ዓለምን የመዞር ታላቅ ሰው የመሆን ሀሳቧ ሁሉ ተቀይሮ “እንዴት ነው ለወገኔ የምደርሰው?” በሚል ሀሳብ ተተካ። ከገንዘብ በላይ የሰው ልጆችን ነፍስ ለማትረፍ የሚያስችል በጎ ተግባር ለመሥራት ቆርጣ ተነሳች።

በስዊዘርላንድ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን እንዴት እርዳታ መላክ እንደሚቻል ያውቁ ስለነበር ፀሐይ ማግኘት የሚገባትን አካል አገናኝተው ልብሶችና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ወደ ሃገር ቤት እንድትልክ ያደርጓታል። በወቅቱ ሕፃናት ኮሚሽን የሚባል ተቋም ውስጥ የእርዳታ ሥራ የሚሠሩት ሰዎች ልብሱን ተቀብለው በፍጥነት እንዲያደርሱላት ብታስብም ያለው ቢሮክራሲ ግን ባሰበችው ፍጥነት ሊያደርሱላት ባለመቻላቸው ወደ ሃገር ቤት መሄድ እንዳለባት ወስና ሥራ አስፈቅዳ ወደ ኢትዮጵያ መጣች።

ገንዘብና አስፈላጊ ቁሳቁስ ይዛ ወደ ትውልድ ሃገሯ የተመለሰችው ፀሐይ “አንድ 20 ልጆችን ለመርዳት ብፈልግ ከመንግሥት የሚገኘው ድጋፍ ምንድን ነው?” ብላ ስትጠይቅ መሬት እንደሚሰጣትና ከውጭ የሚገቡ እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚቻል መሆኑ ይነገራታል። በዚህም መሥራት ያለባትን ሥራዎች በማሰብ የእርዳታ ማስተባበሪያዎቹ ሰዎች ወደ ወሎ እንደሚሄዱ ስትሰማ ለመሄድ ተነሳች። ተጓዦቹን ተከትላ ቦታው ስትደርስ ያየችው ነገር በጣም አሰቃቂ የነበረ እጅግ የከፋ፣ ለማየት የሚከብድ ሁኔታ ላይ የነበረች መሆኗን ትናገራለች።

መንግሥት የሚያደርግላትን ድጋፍ ማረጋገጫ ደብዳቤ ከያዘች በኋላ ወደ ስዊዘርላንድ ተመልሳ በመሄድ ለወዳጅ ዘመዶቿ በማባዛት አሰራጭታ ስትጨርስ በርካታ ገንዘብ ወደ አካውንቷ መግባት ሲጀምር ለሥራው የሚያስፈልገውን ማቴሪያል በሙሉ በኮንቴነር አስጭና ጅቡቲ ደረሰች። በዛው ጊዜ ደግሞ መንግሥት ቃል የገባላትን መሬት በመረከብ ልጆቹ የሚያርፉበት ቤት ግንባታ ተከናወነ።

የመጀመሪያ በሰላም ሕፃናት መንደር የሚያድጉ ልጆችን ለማምጣት ወደ ወሎ ስትሄድ በርካታ ሕፃናት ተሰልፈው ከዛ ሰቆቃ የሚያስመልጣቸውን ሰው እየተጠባበቁ አገኘቻቸው። ከተሰለፉት ልጆች መካከል የቻለችውን ያህል መርጣ 28 ሕፃናትን በማምጣት ሥራው “ሀ” ብሎ ተጀመረ። ከዛ በኋላ ግን ያየችው ነገር አስከፊ ስለነበር ቤቶችን በማስፋፋት በሦስት ወር ውስጥ ዘጠና ሕፃናትን ወደ ሰላም የሕፃናት መንደር አስገብታ የማሳደጉ ሥራ ተጀመረ።

በወቅቱ ትምህርት ቤት በማሳደጊያው ውስጥ ስላልነበረ በደጃዝማች ወንድይራድ ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን እየላኩ ማስተማር ጀመሩ። ሥራው በአግባቡ እንዲደገፍ በእርዳታ ተሰብስበው ከስዊዘርላንድ የመጡ ልብሶችን ልጆቻቸውን አልብሰው የተረፈውን በመሸጥ በማሳደጊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሥራት ተቻለ። ሕፃናቱን ከማሳደግ ጎን ለጎን በጊቢው ውስጥ አትክልት የመትከል፣ ከብት ማርባት፣ ዶሮ ማርባት ላይ ትኩረት አድርጎ በተቻለው መጠን የልጆቹን የምግብ ፍላጎት በውስጥ ምርት ለማሟላት ተግተው ይሠሩ ጀመር።

የፀሐይ አሳዳጊ አባት ዴቪድ ሮሽሊ የልጇን በሥራው ላይ ትኩረት ማድረግ የበርካታ ሕፃናትን ነፍስ ለማዳን የምታደርገው ሩጫ ስለማረከው ከትውልድ ሃገሩ ስዊዘርላንድ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሕፃናቱ አድገው የቀለም ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የሚማሩበት “ሰላም ዴቪድ ሮሽሊ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ”ን ከፈቱ።

ይህ ማሰልጠኛ ተቋም ለትርፍ ያልተቋቋመና በተለያዩ ሙያዎች ወጣቶችን በጣም በአነስተኛ ክፍያ እስካሁን ድረስ እያሰለጠነ የሚገኝ መሆኑን ተመልክተናል።

ኮሌጁ በአዲስ አበባ ሞዴል ኮሌጅና በስልጠና ጥራቱ በአዲስ አበባ በአይ ኤስ ኦ 9001፡2008 ብቸኛ ሰርቲፋይድ የሆነ ኮሌጅ፣ በኮሌጁ የከባድና ቀላል እንዲሁም የእርሻ መኪናዎች ጥገና ስልጠና ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት፣ በሥራ ፈጠራ እና በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ሞዴል ኢንተርፕረነሮች የሆኑ እና በሃገር አቀፍ የሥራ ፈጠራ ውድድር ላይ ተሳታፊ ከነበሩት ውስጥ ዋኖቹ በዚሁ ኮሌጅ ውስጥ ሰልጥነው የወጡ ወጣቶች መሆናቸውን ተከትሎ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች። ኮሌጁ በተለያዩ ዘርፎች የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከልም በመሆን እያገለገለ እንደሚገኝ ወይዘሮ ፀሐይ ሮሽሊ ነግረውናል።



በሕፃናት መንደሩ ያደጉ ልጆች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሠማርተው መመልከት እጅግ በጣም እንደሚያስደስታቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ፀሐይ ሁሉም ልጆቻቸው ተሳካላቸው የሚባል ባይሆንም፣ የራሳቸውን ድርጅት የከፈቱ ልጆች ብዙም ያልተሳካላቸውን ወንድሞቻቸውን በመሰብሰብ ሕይወታቸው እንዲቃና ለማድረግ ሲታትሩ መመልከት፣ በወንድማማችነትና በእህትማማችነት መንፈስ ሲደጋገፉ ማየት እጅግ በጣም የሚያስደስታቸው መሆኑን ወይዘሮ ፀሐይ ትናገራለች።

ወይዘሮ ፀሐይ ስላልተሳካላቸው ልጆቻቸው ስታወራ በርህራሄና በእናትነት አንጀት፣ በ”እንዴት ይሁን?” በሚል መንፈስ ውስጥ ሆነው ሲሆን አድገው ተምረው ማቋቋሚያ ተሰጥቷቸው ከግቢው የተሸኙት ልጆች፣ የተለያዩ ሱሶች ውስጥ ገብተው፣ ገንዘብ አልበቃ ሲላቸው ደግም ተመልሰው ያደጉበት ቤት ደጅ ላይ ስትመለከታቸው፣ ለእናት ምን ትልቅ ቢሆን ልጅ ልጅ ነውና ዳግም ተቀብለው አጥበው፣ አልብሰው፣ አብልተው ሌሎቹ የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ልጆች እንዲያግዟቸው እንደምታደርግ ታስረዳለች።

ከተሳካላቸው ልጆቻቸው መካከል ባሕር ዳር ከተማ ውስጥ ትልቅ ፋሲል ኢንጂነሪንግ የሚባል የግል ኢንቨስተር ልጃቸው ልጆቹ ከሱስ የሚወጡበትን መንገድ በማስተካከል ዳግም የተቃና ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ በሚያደርገው ጥረት እንደሚያመሰግኑት ይናገራሉ።

ሌሎቹ ልጆች ተምረው ሲያጠናቅቁ ቤታቸውን ማገልገል ከፈለጉ ተወዳድረው መግባት የሚችሉበት ሥርዓት ያለ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግቢው የራሱን ገቢ በራሱ ለመሸፈን በሚያደርገው ጥረት ሬስቶራንት ከፍተው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ ክሊኒክ፣ ትምህርት ቤት፣ የግቢው የአስተዳደር ሥራና ሌሎች ዘርፎች ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ።

እያንዳንዱ የበጎ አድራጎት ሥራ የተሳካ እንዲሆን በስዊዘርላንድ ያሉ ዘመዶቿና ጓደኞቿ አስተዋፅኦ ከፍ ያለ እንደነበረ የምትናገረው ወይዘሮ ፀሐይ በወቅቱ በሃገሪቱ ውስጥ የነበሩት ባለስልጣናት ትልቅ ትብብር በማድረግ ለሥራዋ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ትናገራለች።

በፈቃደኝነት ለማስተማር፣ በሙያቸው ለመርዳት የሚመጡት የስዊዘርላንድ ዜጎች በማሳደጊያው ውስጥ በተዘጋጀላቸው ክፍል በመቀመጥ፣ እንደ ኢትዮጵያዊ በመኖር ሲያገለግሉ የሚቆዩ ሲሆን ይዘው የመጡትን እቃ ለማሳደጊያው ሰጥተው የተለያዩ ባህላዊ ሻርፖችን፣ ባህላዊ ምግቦችን ወደ ስዊዘርላንድ በመውሰድ ተሽጠው ለማሳደጊያው ድጎማ እንዲሆን የሚያደርጉበት ሁኔታ እንደነበር ያስታውሳሉ።

አሁን በስዊዘርላንድ የተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት ያለ ሲሆን የወይዘሮ ፀሐይ ታናሽ እህት ኃላፊነቱን ወስደው ይሠራሉ፣ የወይዘሮ ፀሐይ የመጀመሪያ ልጅ ሄኖክም የቦርድ አባል ሆኖ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ፀሐይ ስዊዘርላንድ ከመሄዷ በፊት ቤተሰቦቿ የሚያረቡትን ዶሮ ለየሱፐርማርኬቱ የማከፋፈል ሥራ ላይ እያለች የተዋወቀችው አንድ የሂሳብ ሠራተኛ ዳግም እርዳታ ለማድረግ ወደ ሃገሯ ስትመለስ በአጋጣሚ ተገናኝተው ለትዳር እንደበቁ ትናገራለች። ይህ ሰው የኤርትራ ዜግነት የነበረው ሲሆን ሶስት ልጆችን ካፈሩ በኋላ መለያየታቸውን ታስረዳለች።

የአብራኳ ክፋይ የሆኑት ሄኖክ፣ ዳንኤልና ሚካኤልም አሁን በስዊዘርላንድ የሚገኙ ሲሆን ሁሉም ለወግ ማዕረግ የበቁ የእናታቸውን በጎ ተግባር ለማስቀጠል የሚታትሩ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ወይዘሮ ፀሐይ እርዳታ በጀመረች ጊዜ አካባቢ ሙዳይ ይዘው ቤተክርስቲያን አካባቢ እየለመኑ ለራሳቸው ሳይኖራቸው የብዙዎች እናት የሆኑትን አበበች ጎበናንም ካላት ላይ በማካፈል አግዛቸው እንደነበረ ይነገራል።

ሰጥቶ የማይነጥፍ እጅ ራርቶ የማይደክም ልብ ባለቤቷ ወይዘሮ ፀሐይ በትምህርት ራሴን ላሳደግ እንኳን ሳትል፣ ለዘመናት ለሌሎች ብርሃን ስትሆን ኖራለች። ፀሐይ ገና በልጅነቷ ጀርመን ትምህርት ቤት እስከ ሰባተኛ ክፍል ብቻ የተማረች ሲሆን፣ በተለያዩ ኮርሶች ራሷን ከማጠናከር በስተቀር፣ ምንም ዓይነት የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም አለመከታተሏን ታስረዳለች። ጊዜዋን በሙሉ ልጆቿን በማሳደግ ሥራ ተጠምዳ የኖረች ሰው ነች።

“እማማ ፀሐይ አንቺ ካለፍሽ በኋላ የዚህ መንደር መጨረሻ ምን የሚሆን ይመስልሻል?” ስንል ላነሳንላት ጥያቄ ስትመልስ “ይህ ቤት በርካታ ጠንካራ ልጆችን ያፈራ፣ በጠንካራ የአስተዳደር ሥርዓት የሚመራ ሲሆን እኔም ሞቼ ስሜን እያስጠራ ወላጅ ለሌላቸው ወላጅ፣ ደጋፊ ለሌላቸው ደጋፊ በመሆን ይቀጥላል” ብላለች።

አሁን ልጆችን ተቀብሎ ከማሳደግ ባሻገር ልጆቻቸውን የሚይዙላቸው አጥተው በችግር የሚቆራመዱ እናቶችን፣ ልጆቻቸውን ተቀብሎ በማቆየት የዕለት ሥራቸውን ሠርተው እስኪመለሱ ድጋፍ የሚሰጡ መሆኑን ተናግረዋል። በድርጅቱ በርካታ ሴቶች በነፃ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመውሰድ በሙያቸው ሥራ የሚያገኙበት ሁኔታም መመቻቸቱን ትናገራለች።

በመንደሩ የሚሠሩ ሠራተኞችም ሆኑ በእማማ ፀሐይ እጅ ያደጉ ልጆቻቸው ስለ እማማ ፀሐይ ሲጠየቁ ከቃሎቻቸው ቀድሞ እንባቸው እየፈሰሰ “የእሷን ደግነት በቃላት መግለፅ አይቻልም፣ የተፈጠረችው ለመስጠት ነው። ለመስጠት የተሰጠች ስለሆነ ፈጣሪ እድሜና ጤና እንዲለግሳት ከመመኘት ያለፈ ቃል የለም” ሲሉ ነው የሚደመጡት።

በአንድ ሙሉ መጽሐፍ ተተርኮ የማያልቀውን የእማማ ፀሐይን ታሪክ በዚህ አጭር ጽሑፍ ተርኬ ባልጨርሰው ስማቸው ከሥራቸው ቀድሞ የሚጠራ ከባለ ወርቅ ልቦች መካከል አንዷ፣ ኢትዮጵያዊቷ ማዘር ቴሬዛ የሚል ስያሜ ያንሳቸዋል ለማለት ደፍሬያለሁ።

እማማ ፀሐይ ስለልጆቻቸው ስትናገር “ልጆቼ በታላላቅ የመንግሥት ኃላፊነት ላይ ተመድበው ሃገርንና ሕዝብን በማገልገል ላይ መገኘታቸውን ሳስብ ደስታ ይሰማኛል። ከነዚህም በተጨማሪ የራሳቸውን ትልልቅ የቢዝነስ ተቋሟት ከፍተው ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች የሥራ እድል የፈጠሩ መኖራቸው ደግሞ ይበልጥ ያኮራኛል።”

“በመንደሩ አድገው የራሳቸውን ኑሮ ከመሠረቱት የቀድሞ ልጆቻችን ጋር አሁንም ግንኙነት አለኝ፣ የተለያዩ የእናትነት ፍቅር መግለጫ ስጦታ ያበረክቱልኛል። በአንድ ወቅት የነበረብኝን ቀሪ የመኖሪያ ቤት እዳ እኔ በማላውቀው መንገድ አሰባስበው ከፍለውልኝ ደረሰኙን የሰጡኝ እለት ልቤ እጅግ በጣም ነው የተነካው። ያሳደኳቸውን ልጆች ከአብራኬ ከወጡት በላይ እወዳቸዋለሁ” ብላለች።

የሰው ልጅ አንዱ ለመስጠት አንዱ ለመቀበል ይፈጠራል፣ የፈጣሪ ሥራ አይመረመር ነውና ይህንን ድንቅ ጥበቡን በእማማ ፀሐይ እናትነት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጆች ልጅነት ያስተሳሰረ ፈጣሪ አሁንም በሃገራችን በተፈጠረው ሰላም ማጣት ያለ ወላጅ የቀሩትን ልጆች ሰብሳቢ ይዘዝላቸው። ያለ ጧሪ፣ ቀባሪ የቀሩትንም ጧሪ ቀባሪ ይለግስልን። ሃገራችንን ሰላም አድርጎ ወደ አንድነቷ ይመልስልን፣ በሚለው የእማማ ፀሐይ መልዕክት ቆይታችንን አብቅተናል።

# የምስራቁ ማኅበረሰብ ነፀብራቆች

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የቅርስ ሃብቶች በስፋት ከሚገኙባቸው ቀዳሚ አገራት ተርታ ትመደባለች። ይሁን እንጂ እነዚህን ሃብቶች በሚፈለገው መጠን የማስተዋወቅ፣ የማልማትና ከሃብቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ አቅም ግን አሁንም ድረስ እንዳልጎለበተ ይታመናል። ይህን ለመቅረፍ መንግሥት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየሠራ መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልፅ ይሰማል።

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ተከብሮ ያለፈው የክርስቶስ ልደት (ገና) በዓልን ምክንያት በማድረግ መላው ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገራቸው እንዲገቡና ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሃብቶችን እንዲጎበኙ፣ ሃገራቸውን እንዲያውቅና በተለያዩ አማራጮች ድጋፍ እንዲያበረክቱ በመንግሥት ጥሪ ተደርጎ ነበር። በዚያ መሠረት ገናን በላሊበላ፤ ጥምቀት በጎንደር በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ አልፏል። ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንም ሃገራቸውን አውቀው ለቀሪው ዓለም እንዲያስተዋውቁ እድል የፈጠረ ነበር።

በዚህ በያዝነው ወር ደግሞ "ከኢድ እስከ ኢድ" በሚል መርሐ ግብር በውጪ ሃገራት የሚገኙ ዲያስፖራ የእስልምና እምነት ተከታዮች በተመሳሳይ የረመዳን ፆምና ፍቺን ተከትሎ ወደ ሃገራቸው እንዲገቡና የኢትዮጵያን የባህልና ቱሪዝም ሃብቶች እንዲጎበኙ፣ በታላቁ አፍጥር ሥነሥርዓት ላይ እንዲታደሙ፣ "መረዳዳት፣አንድነትና ኅብረትን" በሚያጠናክሩ መርሐ ግብሮች እንዲሳተፉ እየተደረገ ይገኛል። ከዚህ መርሐ ግብር መካከል በሐረሪ ክልል በልዩ ሁኔታ የሚከበረው የሸዋሊድ በዓል ይገኝበታል።

በሐረሪ ክልላዊ መንግሥት "ከኢድ እስከ ኢድ" በሚል መርሐ ግብር ዝግጅት በተካሄደበት ወቅት የባህል ፌስቲቫል ተካሂዶ ነበር። የዝግጅት ክፍላችንም ይህን ታላቅ ሃገራዊ ጥሪ በማስመልከት የምስራቁ ክፍል ባህላዊ ሃብቶች በተለይ ደግሞ የሐረሪ ብሔረሰብ አልባሳት፣ ተወዳጅ ምግቦችና መጠጦችና ጌጣጌጦችን ልናስተዋውቃችሁ ወደናል። ይህን ባህላዊ ሃብትም የሐረሪ ክልል ባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ተወለዳ አብደሽ ገለፃ አድርገውልናል።





የሐረሪ ብሔረሰብ መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ጌጣጌጦች ለሱ፣

### የሐረሪ ብሄረሰብ መገለጫዎች

የሐረሪ ብሔረሰብ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች አሉት። ከባህላዊ ምግቦች መካከል ከማሽላና ከበቆሎ እንዲሁም ከስንዴ ዱቄት የሚዘጋጁ ኡኻት እና ጡፍጡፍ በመባል የሚታወቁ እንጀራዎች ይጠቀሳሉ። ማባያ ወጦችን በተመለከተ ሒልበት መረኽ በተለምዶ የአብሽ ወጥ እየተባለ የሚጠራው አብዛኛውን ጊዜ በሐረሪዎች ቤት የማይጠፋ ነው። ይህ የወጥ ዓይነት በኡኻት ተፈትፍቶ የሚበላ ሲሆን ለትልልቅ እንግዶች ፤በበዓላትና በሠርግ ጊዜ በቀዳሚነት ከሚቀርቡ የምግብ አይነቶች የሚጠቀስ ነው። ሌላው «አጥ መረኽ »ከፍተኛ ክብር ለሚሰጣቸው እንግዶች የሚዘጋጅ የሒልበት መረኽ አይነት ወጥ ነው። አጥ መረኽ በአዘገጃጀቱ ከሒልበት መረኽ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በግብዓት ደረጃ ቅልጥም ተሰባብሮ ከነመቅኔው ይጨመርበታል። የተመረጡ የሥጋ ክፍሎች እንደምላስ እና ሰንበር እንዲሁም ድንች ሳይላጥ የሚጨመር በመሆኑ ይለያል። ይህ የወጥ አይነት የተለየ ጣዕም ያለው ተወዳጅ የሐረሪዎች ምግብ ነው። አቅሌል መረኽ ከሥጋ የሚዘጋጅ ቀይ የጥብስ ወጥ ሲሆን በኡኻትና ጡፍጡፍ እንዲሁም ከሩዝ ጋር ይበላል። አቅሌል መረኽ የሐረሪዎች የዘወትር ምግብ ቢሆንም በሠርግ እና በበዓላት ወቅትም ይዘጋጃል። ዱባ መረኽ ከዱባ የሚዘጋጅ ወጥ ሲሆን በኡኻት የሚበላ ነው። ሳፍ መረኽ ከሥጋ የሚዘጋጅ ወጥ ሲሆን በኡኻት ይበላል። በበዓላት እና በሠርግ ወቅት እንዲሁም ለእንግዶች ይቀርባል። ከባብ መረኽ ከተፈጨ ሥጋና እንቁላል በወጥ መልክ የሚዘጋጅ ነው። በበዓላት እና በሠርግ ወቅት ለመስተንግዶ ከሚቀርቡ የሐረሪዎች ባህላዊ ምግብ መካከል ተጠቃሽ ነው።

**ዙሑቅ :-** የስንዴ ዱቄት ቢጫ ማቅለሚያ (ሲቆ) ተጨምሮበት ከተቦካ በኋላ በስሱ በምጣድ የሚጋገር የቂጣ አይነት ሲሆን በተቀመመ ወጥ ተለቅልቆ ይዘጋጃል።

**ወቃሲም:-** የተከተፈ ሥጋ በተለያዩ ቅመማ ቅመምና ማጣፈጫዎች ታሽቶ በደንብ ታጥቦና ተዘጋጅቶ በደረቀ የበሬ አንጀት ውስጥ አስገብቶ ከተቋጠረ በኋላ በጭስ እና በእሳት ወላፈን እንዲበስል ወይም እንዲደርቅ በማድረግ የሚዘጋጅ ነው። ይህ ባህላዊ ምግብ እንደ ቋንጣ ተሰቅሎ የሚቀመጥ እና ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችል የምግብ አይነት ነው፤

**ሑል መረኽ:-** ከሀበሻ ጎመን የሚዘጋጅ ወጥ ሲሆን በኡኻት ወይም ጡፍጡፍ ይበላል።

**ሚጣድ ጥብስ:-** የተከተፈ ሥጋ በምጣድ በመጥበስ የሚዘጋጅ ነው።

### ጣፋጭ ምግቦች (መሸባብር)

ሐረሪዎች ከተጠቀሱት ባህላዊ ምግቦች በተጨማሪ ከሰሊጥ ፣ ከስንዴ ዱቄት፣ ከሽምብራ ዱቄት፣ ከተለያዩ ማጣፈጫዎችና ቅመሞች እንዲሁም ከማር እና ከስኳር ጣፋጭ ብስኩቶችን ያዘጋጃሉ። እነዚህ ምግቦች ረጅም ጊዜ መቆየት የሚችሉና በማንኛውም የሐረሪ ቤት የማይጠፉ ሲሆኑ፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ለመመገብ አመቺ ናቸው።በተለይም እንግዳ ሲመጣ አዲስ ምግብ ማዘጋጀት ሳያስፈልግ ለማስተናገጃነት ይቀርባሉ። እነዚህ ዋና ዋናዎቹ ጣፋጭ ብስኩቶች የሚከተሉት ናቸው።

**ሙጠበቅ-**ተፈትጎ የተቆላ ሰሊጥ በቀለጠ ማር ትኩሱን ተድቦልቡሎ የሚዘጋጅ ጣፋጭ ምግብ ነው።

**ሰበዘይነባ :-** ስንዴ ዱቄት ላይ ስኳር ፣ ጥቁር አዝሙድ ፣ ቅቤ ተቀላቅሎ ትንሽ ውኃ ተጨምሮበት ከታሸ በኋላ በትንሽ በትንሹ እየተቆነጠረ በስፌት (አፉፍቱ) ቅርጽ ወጥቶለት በዘይት ይጠበሳል። ጣፋጭ ብስኩት ነው።

**ቡንቱር:-** ስንዴ ዱቄት ላይ ትንሽ ስኳር ፣ ጥቁር አዝሙድ ፣ ቅቤ ተቀላቅሎ ትንሽ ውኃ ተጨምሮበት ከታሸ በኋላ በአነስተኛ የሎሚ መጠን እንደ ዳቦ ቆሎ እየተድበለበለ በዘይት ይጠበሳል። ከዚያም በማር ተለውሶ ይቀርባል። ቡንቱር በረመዷን የጾም ወር ከወንድ ቤተሰብ ለታጨች ልጃገረድ ቤተሰብ ጫት ሲላክ በምላሹ ከሴት ቤተሰብ ተዘጋጅቶ የሚላክ ነው። ቡንቱር ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችል ጣፋጭ ብስኩት ነው።

**ባጃይ:-** ሽርክት የሽምብራ ዱቄት ለተወሰነ ሰዓት ውኃ ውስጥ ከተዘፈዘፈ በኋላ ቀይ እና ነጭ ሽንኩርት ፣ **ባሃሮ** ፣ ቃሪያ ፣ ከሞን ፣ ጨው ተጨምሮበት በትንንሹ እየተድቦለቦለ በዘይት ተጠብሶ የሚዘጋጅ ስኳርነት የሌለው ብስኩት ነው።

**ኹረይባ :-** ነጭ ዱቄት በዘይት፣ ሄል፣ ቀረፋ እና የተፈጨ ስኳር ከታሸ በኋላ በቅርጽ ማውጫ ተቆራርጦ በባትራ ይጠበሳል። ሙሉ በሙሉ የኩኪስ አይነት ባህሪ ያለው ጣፋጭ ብስኩት ነው።

### ባህላዊ መጠጦች

ሐረሪዎች ከአኗኗራቸው፣ ከአመጋገባቸው፣ ከሥራ ባህል እና እምነታቸው ጋር የተያያዙ የተለያዩ ባህላዊ መጠጦች አሏቸው። እነዚህ መጠጦች በማንኛውም ሰዓት አሊያም በዓላት እና ሠርግን በመሳሰሉ ማኅበራዊ ክንዋኔዎችና ሥነ-ሥርዓቶች የሚዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ። በአጠቃላይ መጠጦቹ ተፈጥሯዊ ይዘት ያላቸው የወተት፣ የማር፣ የፍራፍሬ፣ የቡና እና የመሳሰሉት ውጤቶች ናቸው። የሻይ እና የቡና ባህሪ ያላቸው ትኩስ መጠጦች አሊያም በቀዝቃዛ የሚጠጡ የለስላሳ አይነት መጠጦች ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ።

ትኩስ መጠጦች- **ሐሽር ቃሕዋ፡-** ከቡና ጀንፈል ላይ ውኃ፣ ሻይ ቅመም እና ትንሽ ጨው ተጨምሮበት ለሠርግ፣ ለበዓላት እና ለእንግዳ የሚዘጋጅ እንዲሁም ዘወትር የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ ነው።

**ቁጢ ቃሕዋ፡-** ከቡና ቅጠል የሚዘጋጅ የሻይ አይነት ነው። እንደ ሐሽር ቀሕዋ ሁሉ ውኃ፣ የሻይ ቅመም እና ጨው ተጨምሮበት ይጠጣል። የመጠጫ እቃዎቹም ሆነ አቀራረቡ ከሐሽር ቀሕዋ ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ዱስ ቃሕዋ፡-** በማር ተብጥብጦ የሚዘጋጅ ሻይ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ለእንግዳ የሚቀርብ ነው።

**ቀዝቃዛ መጠጦች-** ብርዝ፡- ማር በውኃ በመበጥበጥ የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ ነው። ከተዘጋጀ በኋላ ከቆየ ስለሚፈላና የአልኮልነት ባህሪ ስለሚይዝ ማሩ እንደተበጠበጠ ወዲያውኑ ይጠጣል። **ሴሳው ሸርባት፡-** የተጨመቀ ሎሚ ውኃ፣ ስኳር፣ ሄልና ሌሎች ቅመማ ቅመሞች ተጨምረውበት እንዲሁም ዕርድ ወይም ሌላ ማቅለሚያ ከተደረገበት በኋላ ይዘጋጃል። ይህ ባህላዊ መጠጥ ለመድኃኒትነት ሲወሰድ ወዲያውኑ እንደተዘጋጀ ይጠጣል። የሐረሪ ሴቶች የተለመደ መጠጥ ከሆኑት መካከል የሎሚ ጭማቂ ላይ ውኃና ስኳር ተጨምሮበት የሚዘጋጅ መጠጥ ነው። **ዱስ ሚይ፡-** ማር እና ስኳር በውኃ ተበጥብጦ ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት የሚዘጋጅና ዘይት የሚመስል መልክ ያለውና በሠርግ ወቅት ከሴቷ ሙሽራ ቤት ወደ ወንዱ ሙሽራ ቤት የሚወሰድ ባህላዊ መጠጥ ነው። እነዚህ የተጠቀሱ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች በአብዛኛው እንደተገለጸው በበዓላትና በተለያዩ ማኅበራዊ ክንዋኔዎችና ሥነ-ሥርዓቶች ወቅት የሚጠቀሙባቸው ቢሆንም እንደአስፈላጊነቱ ለዘወትር አገልግሎት ይውላሉ።

### አልባሳትና ጌጣጌጥ

የሐረሪ ብሔረሰብ የማንነቱ መገለጫ የሆኑ የወንዶችና የሴቶች ባህላዊ አልባሳት፣ የአጊያጌጥ ሥርዓት አለው። አለባበሱም ሆነ አጊያጌጡ ዕድሜንና የዕድሜ ሽግግርን መሠረት ያደረገ ነው። ወንዶች ልጆች እስከ ሰባት ዓመት የዕድሜ ክልል የሚለብሱት ቆሎ (ቀሚስ የመሰለ ልብስ) ነው። ከዚህ ዕድሜ በኋላ «የእስላም ወይም ገናፊ የሚባል ነጭ ሱሪ እና እንግሊዝ ቅድ የሚባሉ ሱሪዎችን ይለብሳሉ። እያደጉ ሲሄዱ ጉዱር ቀሚስ (ነጭ ጀለቢያ) ለብሰው ከላዩ ላይ ሰደርያ (ኮት) ይደርባሉ። በራሳቸውም ላይ ኢማሙት ወይም ጥምጣም ይጠመጥማሉ። በባህሉ መሠረት እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ሙሉ ሰው ሆነዋል ማለት ነው። ሌላው ከአልባሳት የሚጠቀሰው ጌይ ከሎይታ (የሐረሪ ኮፍያ) ነው። በብሔረሰቡ የሚታወቁ የተለያዩ የኮፍያ ዓይነቶች ያሉ ሲሆን፣ በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል ጌይ ከሎይታ አንዱ ነው። ጌይ ከሎይታ የከተማ ኮፊያ ማለት ሲሆን በአሠራሩ ነጭ የሚበዛበት ሆኖ በማንኛውም ጊዜ የሚደረግ ነው።

ሌላኛው አሩዝ ከሎይታ የሚባለው ነው። አሩዝ ከሎይታ የሐረሪዎች ባህላዊ ኮፍያ በመባል ይታወቃል። ኮፍያው አብዛኛው መደብ ነጭ ሆኖ በተለያየ ቀለም ባለው ክር በዲዛይን የተጠለፈበት ነው። ይህ ኮፍያ የሙሽሮች ኮፍያ ተብሎ ይታወቃል። በሰርግ ጊዜ ሙሽሮችና ሙዜዎች ይደምቁበታል።

የሴቶች አልባሳትና አለባበስን በተመለከተ ከወንዶቹ አንጻር ስናየው በተለያየ ኅብረ ቀለማት ያሸበረቀና ማራኪ ነው ማለት ይቻላል። ከአለባበስ አንጻር ሴቶች በወጣትነት ዕድሜያቸው ጌይ ገናፊ የተባለ ባህላዊ ሱሪ ይለብሳሉ። ይህ ባህላዊ ሱሪ ከስር ጠባብ ሆኖ ከላይ ሰፋ ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው። ሌላው ከጌይ ገናፊ በላይ የሚለበስ ቀሚስ አጥላስ ይባላል። ይህን ልብስ የሚለብሱት ሙሽሮች፣ በቅርብ ያገባች ‹ሐታም› የምትባል የሐረሪ ሴትና አልፎ አልፎ የብሔረሰቡ እናቶች ናቸው። በእድሜ የገፉ እናቶች ሺአሽቲ ሸለል የሚባለውን ባለ ጥቁር ቀለም ልብስም ይለብሳሉ።

**ጠይ እራዝ፡-** የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ጥቁር ልብስ ማለት ነው። ነገር ግን ሁሉም ጥቁር ቀለም ያለው ልብስ በዚህ ስያሜ አይጠራም። የ"ጠይ ኢራዝ" የራሱ ዲዛይን ያለው ባህላዊ ልብስ ነው። ይህን ልብስ የሚለብሱት ያገቡ እና የዕድሜ ባለፀጋ የሆኑ እናቶች ናቸው። ጠይ እራዝ ከፊትና ከኋላ (በሁለት መልክ) ተገልብጦ ሊለበስ የሚችል በሁለት ዓይነት ቀለም የሚሰራ ቀሚስ ነው። ጠይ እራዝ ከአንዱ በኩል ጥቁር ሆኖ በሌላኛው ደግሞ ከላይ ቀይ ሆኖ ከታች ጥቁር የሆነና በጥልፍ ስራ ያጌጠና የተዋበ ነው። የሐረሪ ሴቶች ወደሰርግ ቦታ ሲሄዱ ከላይ ቀይ ከታች ጥቁር በሆነው በኩል ለብሰው ይሄዳሉ። ይህንን ቀሚስ እንደለበሱ በመንገድ ላይ እንደአጋጣሚ ለቅሶ ቢሰሙ ልብስ ለመቀየር ወደቤት አይመለሱም። ያንኑ የለበሱትን ልብስ በጥቁሩ በኩል ገልብጠው ለቅሶው ቦታ ይደርሳሉ።

ከጌጣጌጥ አኳያ የሐረሪ ብሔረሰብ መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ጌጣጌጦች አሉ። ከእነዚህም አንዱ ወቅሪ ሲሆን የሚሠራው ከብር ነው። ወቅሪ ከላዩ ላይ የተለያዩ ዲዛይኖች የሚደረግበት አሠራሩ እንደ ሀብል አንገት ላይ ተንጠልጣይ ጌጥ ነው። ጌጡ ደረት እላይ የሚቀመጥ በአንድ በኩል የሚከፈትና የሚዘጋ ክዳን እንዲኖረው ተደርጎ የተሠራ ስለሆነ ውስጡ ለተለያዩ መኳኳያዎች መሀረብንም ጭምር ለመያዝ ያገለግላል። ወቅሪን ልጃገረዶች ካህፋያ የሚባል ቁርዓን ሲያጠናቅቁ ያደርጉታል። በቅርቡ ያገባች ሴት (ሐታም) እስከምትወልድ ድረስ ታጌጥበታለች። ከዚህ በተጨማሪም ሠርግ ቤት ሲሄዱ ያጌጡበታል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያ የምርጫ ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

ልክ በዛሬዋ ዕለት እሁድ እና በዛሬዋ ቀን ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ነበር ኢትዮጵያ ታሪካዊውን ምርጫ ያደረገችው። ምርጫ 97 እየተባለ ሁሌም ይጠቀሳል። ይህ ምርጫ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። ስለምርጫ ሲወራ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የፖለቲካ ጉዳይ ሲነሳም ምርጫ 97 ይነሳል።

ይህ ቀን ታሪካዊ የሆነበት ምክንያት፤ ከዚያ በፊትም ከዚያ በኋላም ከተደረጉ የኢሕአዴግ ምርጫዎች የተሻለ አሳታፊ ስለነበር ነው። አሳታፊ ሆኖ ጀምሮ ግን ሁዋላ ላይ ወደ ደም አፋሳሽነት በመቀየሩም ነው።

ይቺ ታሪካዊ ቀን በኋላ ደግሞ «ግንቦት ሰባት» የሚባል የፖለቲካ ፓርቲ እንዲፈጠር አደረገች። ይሄው ፓርቲ የኢሕአዴግ የውስጥ እግር እሳት ሆኖበትም ነበር፤ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ግንቦት ሰባት ታሪካዊ ስም ለመሆን በቅታለች። እኛም በዛሬው ሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም እና እሱን ተከትለው የነበሩ ሁነቶችን እናስታውሳለን።

ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን መግዛት ከጀመረ/ማስተዳደር ለእሱ አይሆነውም/ ከ14 ዓመታት በኋላ የ1997ቱ ምርጫ መሠረታዊ የአስተዳደር ለውጥ እንዲያመጣ የተገደደበት የመጀመሪያው ጊዜ ነው። በምርጫ 97 ብዙ ነገሮች ተቀይረዋል።

ይህ ምርጫ ከመካሔዱ በፊት የፖለቲካ ምሕዳሩ የሰፋበት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተጠናከሩበት፣ ሐሳብን በነጻነት መግለጽ እምብዛም ያልተገደበበት፣ የፖለቲካ እስረኞች እስር ቤቶቹን ያላጨናነቁበት ጊዜ ነበር።

ይህ ሁሉ ግን በምርጫው ውጤት አጥቢያ ገዢው ፓርቲና ዋና ዋናዎቹ ተቃዋሚዎች፣ በተለይም ቅንጅት ሲወዛገቡ በአንድ ጊዜ ወደ ተቃራኒው ሁኔታ ተለወጧል። ከ97ቱ ምርጫ በኋላ ቢያንስ ለስምንት እና ዘጠኝ ዓመታት ያህል የአደባባይ የተቃውሞ ሰልፍ አልተካሔደም። የዋነኛዎቹ ተቀናቃኞች የቅንጅት ለአንድነት እና ለፍትሕ አመራሮች፣ የሲቪል ማኅበራት አባላት እና ጋዜጠኞች በገፍ እና በግፍ ታሰሩ። የፖለቲካ ምኅዳሩን የሚያጠቡ ሕግጋት ወጡ። የፖለቲካ ድርጅቶች ተዳከሙ፣ በርካታ ብዙኃን መገናኛዎች ተዘጉ፣

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ገጽታም በዓለም ፊት ተበላሸ። ከምርጫ 97 በኋላ የተከተለው ፖለቲካዊ አፈና «ኢሕአዴግ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚፈልገው ራሱ ምርጫ የሚያሸንፍ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ብቻ ነው» በሚል እንዲተች አደረገው።

የምርጫውን ዕለት ክስተቶች በዕለቱ አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ያስታውሱታል። አንዳንዶችም ራሱን የቻለ መጽሐፍ ጽፈውበታል። ከእነዚህም አንዱ ኢሕአፓ መሥራችና «ኢትዮጵያ ሆይ» በሚሉት መጽሐፎቹ የሚታወቀው ክፍሉ ታደሰ ነው። ክፍሉ ታደሰ «ግንቦት 7» በሚለው መጽሐፉ በዕለቱ በአዲስ አበባ የተለያዩ ምርጫ ጣቢያዎች ያስተዋለውንና የታዘበውን ለታሪክ ጽፎ አስቀምጧል።

ክፍሉ ታደሰ «ግንቦት 7» በተሰኘው መጽሐፉ፤ ምዕራፍ 5 «ግንቦት 7 ታሪካዊ ቀን» በሚል ርዕስ «ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም 524 የምክር ቤት ወንበሮች ለውድድር ቀረቡ። 23 የሚሆኑት በነሐሴ ወር በሶማሌ ክልል ለሚደረገው ምርጫ ወደ ጎን ተተው።

ግንቦት 7 በተካሄደው ምርጫ ተሳትፌያለሁ። ማን ይናገር ነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ እንደሚባለው፤ ያየሁትን፣ የሰማሁትን፣ የተሳተፍኩበትን ነው የማቀርበው። እኔ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ታሪኩን በሦስተኛ ሰው አድርጌ ላቀርበው አስቤ ራቀብኝ። የእኔ መስሎ አልሰማህ አለኝ፤ እናም በቀጥታ ላቀርበው ወሰንኩኝ» በማለት ደራሲው ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውስጥ የነበረውን ሁነት በቀጥታ በመሳተፍ ያየነውን ነግሮናል።

ማለዳ 12፡00 ተነስቶ መገናኛ ሲደርስ ረጅም ሰልፍ አጋጠመው። ሰልፉ እየተጠማዘዘ ቢያንስ ከ300 ሜትር በላይ እንደሚሆን ይገምታል። ደራሲው የዕለቱን እንቅስቃሴ ማየት ፈልጎ ስለነበር ብዙ የምርጫ ጣቢያዎችን እየተዘዋወረ ተመለከተ። ሁሉም ረጃጅም ሰልፎች ያሉባቸው ናቸው።

ደራሲው ከዚያ በፊት የነበሩ ምርጫዎችንም ያስተዋለ መሆኑን አስታውሶ፣ የዚያን ዕለት የነበረው ተሳትፎ ግን የተለየ እንደነበር ይገልጻል። በነገራችን ላይ መጽሐፉ የተጻፈው ከባለፈው ዓመት (2013) ምርጫ በፊት ስለሆነ ባለፈው ዓመት የተካሄደውን 6ኛውን አገር አቀፍ ምርጫ አይመለከትም።

የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ተስፋ ጥሎበት የነበረ ለመሆኑ፤ የምርጫው



**የምርጫ 97 ሰሞን ግዙፍ የድጋፍ ሰልፎች ታይተውበታል፡፡**

እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ተሳትፎ አስተውሏል። በምርጫው ዕለትም እንደሌላ ጊዜ «ውጣ» እየተባለ ሳይሆን፤ ሕዝቡ በራሱ ተነሳሽነት በነቂስ ወጣ።

በዚህ ዕለት ሕዝቡ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች የሄደው በመንግሥት ካድሬዎች ቅስቀሳ ብቻ ሳይሆን በተፎካካሪ ፓርቲዎችም ቅስቀሳ ነው። በዚያ ምርጫ የምርጫ ካርድ ያላወጡ ዜጎች ተፀፅተዋል።

ምርጫው በዕለቱ ፍጹም ሰላማዊ እንደነበር ደራሲው ይገልጻል። ምንም አይነት አጠራጣሪ እንቅስቃሴ ስላልነበረ ፖሊሶች ደከሟቸው ቁጭ ይላሉ። ሕዝቡም አዛውንትና አካል ጉዳተኞችን እያስቀደመ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሲመርጥ ዋለ። በዕለቱ ከወለደች ገና 15 ቀን የሆናት አራስ፣ ታመው ከአልጋ ላይ የመጡ፣ በሰው ድጋፍ የመጡ... መራጮች እንደነበሩ ደራሲው አስተውሏል።

ምርጫ 97 ብዙ ነገሮችን ያሳየ ምርጫ ነው። በዕለቱ አዲስ አበባ የነበረውን ሁነት ያስተዋሉ ሁሉ የተለያየ ገጠመኝ አላቸው። የምርጫ 97 ታላቅ የሕዝብ እንቅስቃሴና የታየው ተስፋ ግን ምርጫው በተካሄደበት ቀን ሌሊት በአጭር መቀጨት ጀመረ። የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት ይፋ ማድረግ ያለበት ምርጫ ቦርድ ተብዬው መሆን ሲገባው የምርጫው እለት ሌሊቱን ኢሕአዴግ ማሸነፉን ገለጸ። የቅንጅት መሪዎች በበኩላቸው በምርጫው ማሸነፋቸውን ገለጹ።

ከዚህ በኋላ ጸረ ዲሞክራሲ ተግባሩ ተጠናክሮ ቀጠለ። የምርጫው ውጤት ተጭበርብሯል፤ ኮሮጆ ተገልብጧል በሚል ቅንጅትና ደጋፊዎቹ ይጠይቁ ጀመር። ለወራት ሕዝባዊ ቁጣዎች ተቀሰቀሱ። ይህ የሆነው ደግሞ ቅንጅት በተወዳደረባቸው ክልሎችና ከተሞች ሁሉ ነበር።

ኢሕአዴግ ይህን ቁጣ ለማስቆም ያልወሰደው እርምጃ የለም። የምርጫው ውጤት ተጭበርብሯል፤ ኮሮጆ ተገልብጧል በሚል ተቃውሞ የሚወጡትን ሁሉ መደብደብ፣ ማፈስ፣ማሰቃየት አልፎም ተርፎ መግደል ውስጥ ገባ፤ ያፈሳቸውን ሁሉ ወለጋ ውስጥ ወደ ሚገኘውና በደርግ ወቅት ወታደራዊ ማሰልጠኛ ወደ ነበረው ደዴሳ አጎረ።

በዚህ እስር በፖለቲካው ንቁ ተሳትፎ ያልነበራቸው ምንም የማያውቁ፣የአዕምሮ ሕሙማን ሳይቀሩ ታስረው እንደነበር በእስሩ ላይ የነበሩ ይናገራሉ። በዚያም የተገደሉና የሞቱ በርካታ መሆናቸው ይገለጻል። የፓርቲው መሪዎች ወህኒ እንዲወርዱ ተደርገ። ይህ ታሪካዊ ቀን እነሆ በበጎም በመጥፎም እየታወሰ ይኖራል።

## ከሕዝብ ጎን የቆሙት ባለሙያ

**ዋለልኝ አየለ**

ሌላኛው የዚህ ሳምንት ክስተት የፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ሕልፈተ ሕይወት ነው። የእርሳቸው ታሪክም ከኢሕአዴግ ጋር ይገናኛል። በነገራችን ላይ የግንቦት ወር የኢሕአዴግ ታሪክ ነው ማለት ይቻላል። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት፣ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በታሪክ የተወቀሰበት ምርጫ የተካሄደበት እና ግንቦት 6 ቀን በግፍ ሲያሰቃያቸው ከነበሩ ሰዎች አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ያረፉበት ነው።

ፕሬፌሰር አሥራት ወልደየስ የሕክምና ባለሙያ ሲሆኑ በሕወሓት/ኢሕአዴግ በሕዝብ ላይ ይደርስ የነበረውን ግፍ ለመታገል የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም መስዋዕት የከፈሉ ናቸው። የእኝህን ሰው ሕይወት እና የፖለቲካ ውጣ ውረድ እናስታውሳለን።



አሥራት ወልደየስ ከአባታቸው ከአቶ ወልደየስ አልታዬና ከእናታቸው ከወይዘሮ በሰልፍይዋሉ ጽጌ ሰኔ 12 ቀን 1920 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። የአሥራት አባት አቶ ወልደየስ አልታዬ በጸሐፊ ትዕዛዝ ኃይሌ ወልደሥላሴ አስተዳደር ውስጥ በጸሐፊነትና በአስተዳደር ተግባር የተሠማሩ ነበሩ። እናታቸውም በአነስተኛ ንግድ የተሠማሩ ነበሩ። ፕሮፌሰር አሥራት የሶስት ዓመት ሕጻን እያሉ ወላጆቻቸው በፍች ምክንያት ስለተለያዩ ከእናታቸው ጋር ወደ ድሬዳዋ አቀኑ።

አሥራት ድሬዳዋ በነበሩበት ወቅት ጣሊያን ኢትዮጵያን ትወራለች። በዚህ ወቅት በእነ ሞገስ አስገዶምና አብርሃም ደቦጭ ግራዚያኒ ላይ የተደረገ የግድያ ሙከራን ለመበቀል ከግራዚያኒ በተላለፈ በቀል በሶስት ቀናት ውስጥ ብቻ ከ33 ሺህ በላይ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በዶማ፤ በአካፋና በገጀራ ጭምር ተጨፍጭፈዋል። የአሥራት አባት አቶ ወልደየስ አልታዬም እንደ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተጨፍጭፈው በአርበኝነት ሞቱ። እናታቸው ወይዘሮ በሰልፍይዋሉ ጽጌም የባለቤታቸው ሞት ተጨምሮበት ብዙም ሳይቆዩ ታመው ሕይወታቸው አለፈ።

ወላጆቹን በሞት የተነጠቀው ታዳጊ በድሬዳዋ ከአያቱ ጋር አደገ። ቄስ ትምህርት ቤት ገብቶም ጎበዝና ፈጣን ተማሪ ነበር ይባላል። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገባ። አንደኛ በመውጣትም ተሸላሚ ሆነ። በወቅቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ውጤት የሚያጠናቅቁ ወደ ውጭ ይላኩ ስለነበር አሥራት ወደ ግብጽ ተልከው ተከታትለዋል። ከዚያም በስኮላርሽፕ እንግሊዝ አገር ሄደዋል። እንግሊዝ አገር የሕክምና ትምህርት ተምረው ወደ አገራቸው በመመለስ በሕክምና አገልግለዋል።

ዶክተር አሥራት ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የሕክምና ማሰልጠኛ እንዲከፈት በመወትወታቸው ምክንያት የጥቁር አንበሳን ሆስፒታል እውን አደረጉ። የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሲቋቋም የቴክኒክ ኮሚቴውን የመሩት እሳቸው ነበሩ። እ.ኤ.አ በ1965 ዓ.ም የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እውን ሲሆን ፕሮፌሰር አሥራት ተባባሪ ፕሮፌሰር በመሆን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዲን ሆኑ። ከዚያ በፊት በውጭ ባለሙያዎች ነበር።

ፕሮፌሰር አሥራት በደርግ ዘመነ መንግሥት በተደጋጋሚ ዘመቻ የተላኩ ሲሆን፣ የሄዱበትን ዘመቻ በክብር ለመወጣት በቅተዋል። በዚህም መሠረት በ1968 ዓ.ም በቀዶ ሕክምና ሐኪምነት በቃኘው ሆስፒታል አስመራ፤ በ1969 ዓ.ም እንደገና በቃኘው ሆስፒታል አስመራ፤ በ1970 ዓ.ም በራዛ ዘመቻ በቀዳጅ ሐኪምነት እና ቡድን መሪነት በመቀሌ ሆስፒታል፤ እንዲሁም በሰኔ 1971 ዓ.ም በቀዳጅ ሐኪምነት ምጽዋ ዘምተው ግዳጃቸውን ተወጥተዋል። የተለያዩ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ሽልማቶችንም አግኝተዋል።

የደርግ ሥርዓት ተሸንፎ ኢሕአዴግ አገሪቱን በተቆጣጠረበት ወቅት፤ ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓ.ም በተደረገው የሽግግር መንግሥት ቻርተር ውይይት ላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ወክለው ተገኝተዋል፤ በእዚህም ወቅት ነው ፕሮፌሰር አሥራት የኤርትራን መገንጠል አስመልክቶ በተካሄደ ውይይት ላይ «ሃገር ላስገነጥል ተወክዬ አልመጣሁም» በማለት ተቃውሞ ያሰሙት። «ይህ ጉባኤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምንም ጉዳይ ሊወስን፤ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ አይችልም» በማለት ጉባኤው እያደረገው ያለው ውሳኔ ኢ-ዲሞክራሲያዊ መሆኑን አስረግጠው ሞገቱ። በዚህ ንግግራቸውም የተነሳ ከጉባኤው ሲወጡ ብዙ ማስፈራሪያና ዛቻ ተካሄደባቸው።

እንዲህ እንዲህ እያሉ ፕሮፌሰር አሥራት ወደ ፖለቲካው ዓለም ገቡ። የኢሕአዴን አገዛዝ ለመታገል የመላ አማራ ህሕዝብ ድርጅት /መአሕድ/ የተሰኘ ፓርቲ መሥርተው መንቀሳቀስ ጀመሩ። ከኢሕአዴግ ጋር አይጥና ድመት ሆኑ። ኢሕአዴግም እያሳደደ ያሥራቸውና ይፈታቸው ጀመር። ኢሕአዴግ እንቅስቃሴያቸውን ባየ ቁጥር እስርና እንግልቱን አጠናከረው። ለብቻቸው በማሰር ስቃይና መከራም ያደርስባቸው ጀመር።

የእስር አያያዛቸው የከፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በ1972 ዓ.ም የጀመራቸው የልብ ሕመም ተባብሶ እንዲሁም የስኳር መጠናቸው በመጨመሩ ከፍተኛ የጤና ችግር ላይ ወደቁ። ለብዙ በሽተኞች መድኃኒት የነበሩት አሥራት ሕክምና ተከልክለው የበሽታ መጫዎቻ ሆኑ። ከስኳራቸው ከፍ ማለት ጋር ተያያዞ አይናቸው ማየት ተሳነው። ሰውነታቸውም እንደፈለጉ አልታዘዝ አለ። የልብ ድካማቸው ጨመረ።

ሕክምና እንዲያገኙ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይቀር ደብዳቤ ጻፉ። መፍትሔ ግን አላገኙም። የኋላ ኋላ ሲዳከሙ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ቢወሰዱም ሕመማቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ መፍትሔ ሊያገኙ አልቻሉም። በመጨረሻም እ.ኤ.አ ታኅሳስ 27 ቀን 1998 ዓ.ም ወደ ውጭ ሃገር ሄደው እንዲታከሙ ተፈቀደ።

በከፍተኛ ሁኔታ በመድከማቸው አውሮፕላን ውስጥ በሐኪሞች እየታገዙ ወደ ለንደን ሆስፒታል በረሩ። ከ3 ቀናት ቆይታ በኋላ ወደ አሜሪካ ሆስተን አመሩ። በአሜሪካ ቅዱስ ሉቃስ ኤጲስቆጳል ሆስፒታል በነበሩበት ወቅት እንደተሻላቸውና ከልቡ ሲያስባቸው ለነበረው ሕዝብ መልዕክት አስተላልፈው ነበር። ትንሽ እንደተሻላቸው ዘመዶቻቸው ወደሚገኙበት ፊላደልፊያ ከወር በፊት ተዛውረው በነበረበት ወቅት ባልታወቀ ምክንያት ሕመማቸው ተባብሶ ተዳከሙ።

ሞትን ድል ሲያደርጉት የኖሩት ሐኪም ግንቦት 6 ቀን 1991 ዓ.ም ፊላደልፊያ በሚገኘው ፔኒሲለቫኒያ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በዕለተ ዓርብ በተወለዱ በ71 ዓመታቸው አረፉ። በወቅቱ የፕሮፌሰሩን ሞት ትልልቅ የዓለም መገናኛ አውታሮች ሰፊ ሽፋን ሰጥተው ነበር።

# የዝነኞች ገጽ

# የተውኔት ሐኪሙ ዮናስ

(አቤል ገ/ኪዳን)

ባለሙያዎች ወርቃማ ድምጽ ይሉታል ድምጹን። አስገምጋሚ ድምጽ አለው። ሰውነቱን ላየ ሰው ድምጹ ከሱ የሚወጣ አይመስለውም። በዚህም የተነሳ ብዙዎች በትወና የሚያውቁትን ያህል በዚህ ጀሮ ገብ ድምጹ ለይተው ያስታውሱታል። የዛሬው እንግዳችን አንጋፋው ተዋናይ ዮናስ ጌታቸው ነው።

የበረሀዋ ንግስት በምትባለው ድሬዳዋ ከተማ ተወለደ። ወቅቱም ጥቅምት 23 ቀን 1962 ዓ.ም ነው። አባቱ አቶ ጌታቸው ውብሸት እና እናቱ ዘውድነሽ ተፈራ ከወለዷቸው ስድስት ልጆች የመጀመሪያው ዮናስ ሆነ። ከሱ በታች ሌሎች ሁለት ወንዶች እና ሶስት ሴት ልጆች አሉ።

አባት እና እናቱ ነጋዴ ነበሩ፤ ነገር ግን በጊዜ ሂደት የንግዱ ሁኔታ አላዋጣ ሲል ወደ ተቀጣሪነት ዞሩ። አባት ድሬዳዋ ምድር ባቡርን እናት ድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅን ተቀላቀሉ። የመጀመሪያ ልጃቸው ዮናስ ደግሞ የንግድ ሥራውን መሞካከር ቀጠለ። በተለይም 1982 ላይ ብሔራዊ ፈተናን ከወሰደ በኋላ ሥራው ይህ ነበር።

የአራተኛ እና አምስተኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት በክፍል ውስጥ እንደማንኛውም ታዳጊ ይሳተፍበት ከነበረው ሙዚቃና ውዝዋዜ በቀር ለጥበብ ዝንባሌ ኖሮት የማያውቀው ዮናስ፣ ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ /ማትሪክ / ፈተናው በኋላ ግን ያልጠበቀው የጥበብ በር ተከፈተ።

በሚኖርባት ድሬዳዋ ከተማ አጎናፍር ወዳጆ የሚባል የጥበብ ሰው ተውኔት እያዘጋጀ ነበር። ነገር ግን ተውኔቱ ላይ ዋነኛ ተዋናይ የነበረው ልጅ ቴአትሩ ለሕዝብ ሊቀርብ ቀናት በቀሩበት ወቅት ቤተሰቦቼን ልጠይቅ ብሎ ከድሬዳዋ ወደ ትውልድ ስፍራው ይሄዳል።

ይሄኔ የቴአትሩ ደራሲ የሚያደርገው ሰው ግራ ገባው። ስለዚህም ወደ ዮናስ መጣ። ተውንልኝ አለው። ዮናስ ከዚህ ቀደም ስለ ቴአትርም ሆነ ስለ ሌላ የጥበብ ጉዳይ እውቀት ባይኖረውም እሺ አለ። ደራሲው ዮናስን ወስዶ አሸዋ ላይ የመድረኩን ገጽታ ስሎ "ይሄ ሳሎን ነው ፤ ይሄ መኝታ ቤት ነው" ብሎ መግቢያ እና መውጫውን አሳየው። ቃለ ተውኔቱንም በቀናት ውስጥ ከነስሜቱ አጥንቶ ተወነ። ዮናስና ጥበብ ፤ ዮናስ እና ቴአትር ፤ ዮናስና መድረክ ተዋወቁ ፤ ተዋደዱም። ከዚያ በኋላ ትወናው ላይ በረታ። ሌሎች ተውኔቶችንም ሠራ።

ዮናስ እና ቴአትር ድሬዳዋ ላይ የጀመሩት ፍቅር እየጠፈ ሲሄድ ይሳተፍበት የነበረው ወጋየሁ ንጋቱ የተሰኘ የቴአትር ክበብ እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ ያዘ። ስለዚህም ዮናስ እና ጓደኛው ድሬዳዋን ትተው የቴአትርም ሆነ የሌሎች ነገሮች መናኸሪያ ወደነበረችው አዲስ አበባ መጡ።

አንድ ቀንም ወደ ባህል ማዕከል ጎራ አሉ። ሲደርሱ ተዋንያን በሙሉ ልምምድ ላይ ናቸው። ቁጭ ብለው ልምምዱን መከታተል ያዙ። ይሄኔ ደራሲው እና ዋና አዘጋጁ ጌታቸው ታረቀኝ ወደ እነሱ መጣ። ምን እየሠራችሁ ነው ብሎ ጠየቀ። ዮናስ እና ጓደኛውም ከድሬዳዋ እንደመጡ ፤ ቴአትርን እንደሚወዱ እና ቴአትር ማየት ስለናፈቃቸው ወደ እዚህ እንደመጡ ይነግሩታል።

እሱም ጥቂት ጥያቄዎችን ካቀረበላቸው በኋላ የየኔ ቢጤ ገጸ ባህሪ ተውነው እንዲያሳዩ ጠየቃቸው። ተውነው አሳዩት። በማግስቱ ለገጸ ባሕሪው የሚሆን ልብስ ለብሰው እንዲመጡ አዘዛቸው። ለብሰው መጡ። የተውኔቱ አካል ሆነውም ተሳተፉ። ከዚያ በኋላ ሌላ ድርሰት እንዲያጠኑ ሰጣቸው። በ15 ቀን ውስጥ አጥንተው ጨረሱ። 1984 ላይ ያ የተለማመዱት ቴአትር ሃገር ፍቅር መድረክ ላይ ቀረበ። ነገሮች በዚህ ቀጠሉና ዮናስ በተውኔት 50 ብር በወር 200 ብር እየተከፈለው ቀጠለ።

ከዚያም በ1987 ኢ.ም በአዲስ አበባ ቴአትር እና ባህል አዳራሽ ተቀጠረ።በዚያ እየሠራ እያለ ሃገር ፍቅር ቴአትር የደረጃ እድገት ወጣ። በቴአትር እና ባህል አዳራሽ 370 ብር ይከፈለው የነበረው ዮናስም ሃገር ፍቅር በ50 ብር ጭማሪ 420 ብር ተከፋይ ሆኖ ገባ።



የትወና ሕይወቱም ከፍተኛው ደረጃ ላይ ደረሰ።

1989 ላይ ግን ዮናስ ከሚሠራበት ቴአትር ቤት ተሰናበተ። ወደ ትውልድ ቦታው ድሬዳዋም ተመለሰ። ድሬዳዋ ሲመለስ ዝም ብሎ አልተቀመጠም። ሕጻናትን እና ወጣቶችን ሰብስቦ ቴአትር ማስተማር ጀመረ። ቴአትሮች እንዲቀርቡም አደረገ። አንድነት የተሰኘ የቴአትር ክበብም አቋቋመ። ላሳደገችው ድሬዳዋ በሙያው ውለታዋን ለመመለስ ሞከረ።

ከሥራው ከተሰናበተ ከ8 ወር በኋላ ከአዲስ አበባ ተደወለለት። ና ቅጥር ወጥቷል ተባለ። መጥቶ በድጋሚ ተቀጠረ። ከዚያም በኋላ በመሐል ለ5 ዓመታት በሕጻናት እና ወጣቶች ቴአትር ቤት ከነበረው ቆይታ ውጭ ጠቅላላ የሙያ ሕይወቱ በሃገር ፍቅር ቴአትር ቤት ውስጥ ነው።

ዮናስ ተዋናይነቱ ላይ እንከን አይወጣለትም። ከዚህም በላይ ቴአትርን በመጠገን እና በማሳደግ ረገድም ጎበዝ ነው። ይህ ዘርፍ በባለሙያዎቹ አንደበት ሀኪመ ተውኔት (ፕለይ ዶክተር) ይባላል። ተውኔቱ ላይ ያለውን ክፍተት ማስተዋል እና ያንን ጠግኖ የማሻሻል ሥራ ማለት ነው።

በዚህ ዘርፍ በርከት ያሉ ሥራዎችንም ሠርቷል። የዚህ መነሻው አንድ ቀን አለቃው ጌታቸው ታረቀኝ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን የሆኑ ተዋንያን ድርሰት ጽፈው እንዲያመጡ አዘዘ። ጽፈው አመጡ። ከዚያም አስተያየት እንዲሰጥበት ሲቀርብ ሁሉም አንጋፋ ተዋንያን ቴአትሩ ጥሩ ነው አሉ። ዮናስ ግን ቃለ ተውኔቱ ያለበትን ክፍተት ዘርዝሮ 11 ገጽ ሂስ ጽፎ መጣ። ይሄኔ ሁሉም በዮናስ ሀሳብ ስለተስማሙ ለምን እሱ እንደ አዲስ አይጽፈውም አሉ፤ ተሰጠው። በድጋሚ አስተካክሎ ጽፎ አመጣ። የመጀመሪያ የቴአትር ሕክምናውንም በዚህ መልኩ አከናወነ።

**ዮናስ ተዋናይነቱ ላይ እንከን አይወጣለትም። ከዚህም በላይ ቴአትርን በመጠገን እና በማሳደግ ረገድም ጎበዝ ነው። ይህ ዘርፍ በባለሙያዎቹ አንደበት ሀኪመ ተውኔት (ፕለይ ዶክተር) ይባላል**

ቆየና ሌላ ዳና በተሰኘ ተውኔት ላይም ይህን ጥበቡን ተጠቀመ። እንዲህ እንዲህ እያለ በተውኔት ሐኪምነቱ በረታበት። ሌሎችንም ሠራ። ዮናስ እንደሚለው ከሆነ ብዙውን ጊዜ ደራሲዎች ተውኔትን ሲያዘጋጁ ሁሉንም በራሳቸው ልክ ይቃኟቸዋል። በዚህም የተነሳ ገጸባህሪው እና የሚናገረው ንግግር ያለመጣጣም ችግር ያጋጥማቸዋል። ስለዚህም እሱ እንዲህ አይነት ግድፈቶችን ሲያይ በተውኔት ሐኪምነቱ ደራሲውን ከገጸ ባሕሪው የማውጣት እና ገጸ ባሕሪው ራሱን ችሎ እንዲቆም የማድረግ ሥራ ይሠራል። ከዚህም በተጨማሪ ታሪኩ በሚፈለገው ልክ ሴራ ሲጎድለው ፤ ጡዘት ላይ መድረስ ሳይችል ሲቀር ወይም መሰል ቴክኒካዊ ግድፈት ሲኖረው የተሰጠኝን ብቻ ልሥራ ከማለት ይልቅ ተቀብሎ ማስተካከል የሚችለውን ያህል ይሠራል።

የቼዝ ዓለም ፤ የስልጣን ማደጎ ፤ ፎርፌ እና በርካታ ቴአትሮችን በተዋናይነት የሠራው፤ ብዙ ተውኔቶችን ያከመው እና በሬዲዮም ሳቤላ እና ሌሎች ድርሰቶችን በወርቃማ ድምጹ የተወነው ዮናስ በቴሌቪዥንም ብዙዎች ያውቁታል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ይበልጥ የተዋወቀበትም እምአእላፍ በሚል ገጸ ባሕሪ የተወነበት የማለፊያ ጉዞ የተሰኘ የቴሌቪዥን ድራማ ነው።

ከዚያም በኋላ ማን ገደላት ፤ በዚህ መንገድ አለ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት በነበራቸው የመስኮት አጫጭር የቴሌቪዥን ድራማዎች እንዲሁም በጥላሁን ዘውገ እና አለልኝ መኳንንት ይዘጋጁ የነበሩት ስንቅ ተከታታይ አጫጭር የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ በደራሲነት እና በተዋናይነት ተሳትፏል።

ዮናስ ብዙም ያልገፋበት የትወና ዘርፍ የፊልም ትወና ዘርፍ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ እሱ በስክሪፕት ላይ የሚሰጠው ሂስ ነው። ፊልም እንዲሠራላቸው የሚፈልጉት ሰዎች የሚሰጡት እሱ እንዲተውንላቸው የሚፈልጉትን የፊልሙን ክፍል ብቻ ሲሆን እሱ ግን ለመሥራት ከመስማማቱ በፊት ሙሉውን ስክሪፕት እንዲሰጡት ነው የሚፈልገው። በዚህ ከብዙዎች ጋር መስማማት ስለማይችልም ብዙ ፊልሞች ላይ አልተሳተፈም።

ዮናስ እስካሁን ላጤ ነው። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚያነሳው የኑሮውን አለመመቻቸት ነው። ከ1992 ጀምሮ ቤት እንዲሰጠው ለቀበሌ ጥያቄ እንዳቀረበ ነገር ግን ያመለከተበት ቀበሌ ሁሌም ያስገባው ማመልከቻ ጠፋ እንደሚባል ይናገራል። በአሁኑ ወቅት በሚሠራበት ሀገር ፍቅር ከታክስ በኋላ የሚደርሰው ገንዘብ 4100 ብር እንደሆነ የሚናገረው ዮናስ ለቤት ኪራይ 4ሺ ብር እንደሚከፍል ይናገራል። በዚህም የተነሳ አሁን ልጅ በመውለጃ ጊዜዬ አላገባሁም ይላል። ለከርሞው ግን እቅዱ ማግባት እንደሆነ ይናገራል።

ዮናስን የእረፍት ቀንህን በምንድን ነው የምታሳልፈው አልነው። "እኔ ከእሁድ እስከ እሁድ እዚህ ነኝ። ብዙም ማኅበራዊ ሕይወት የለኝም። እዚሁ ተውኔቶችን ስጽፍ ነው የምውለው። "ይላል። እቅዱም ሁለት የሙሉ ጊዜ ተውኔቶችን መጻፍ እና ትዳር መያዝ እንደሆነ ይናገራል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዮናስ በቅርቡ የቴአትር ሕይወቱን አደጋ የሚከት ክስተት አጋጥሞት ሰሞኑን የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት ስቦ ነበር። ነገሩ የተከሰተው ታኅሳስ 28 ቀን 2012 ቀን ነው። እንደተለመደው ሃገር ፍቅር ቴአትር አምሽቶ ወደ ቤቱ ሲሄድ ገዳም ሰፈር በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ በር ላይ በወሮበሎች አንገቱ ላይ ጉዳት ደርሶበት ገንዘቡን እና ስልኩን ይቀማል።

በወቅቱ ከተፈጠረው ክስተት በኋላ መለስተኛ ሕክምና ቢያደርግም፣ በጊዜ ሂደት ያ ገጠመኝ የጉሮሮው አንደኛ ክፍል እንዳይሠራ በማድረጉ በሚፈልገው እና ለመድረክ በሚመጥን መልኩ ድምጽ ማውጣት እንዳይችል በማድረጉ ከሚተውንበት ተውኔትም እንዲወጣ አድርጎታል። በአሁኑ ወቅት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሕክምናውን እየተከታተለ ሲሆን፣ ሐኪሞችም ወርቃማውን ድምጹን ለማቆየት ጥረት እያደረጉ ናቸው። ሕክምናውን በአግባቡ ለመከታተል ግን የሕዝብን ድጋፍ ይሻል።

## ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# ኮርፖሬሽኑ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ለማምረት እየሠራ ነው

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በሕንፃና ቤቶች፣ በመንገድና አየር ማረፊያ፣ በግድብና መስኖ፣ በውሃ መስመር ዝርጋታና ድልድይ ግንባታዎች ላይ ተሠማርቶ በርካታ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው።

ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዋጋ በየጊዜው እየናረ በመምጣቱና አብዛኛዎች የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ከውጪ የሚገቡ በመሆናቸው በዘርፉ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል። ይህንን ተግዳሮት ለመቅረፍና ግንባታዎችን በወቅቱ ለማጠናቀቅ ከውጪ የሚገቡ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በሃገር ውስጥ አምርቶ ለመጠቀምና የውጪ ምንዛሪን ለማዳን እየሠራ ይገኛል። ይህንን እውን ለማድረግም የኮርፖሬሽኑን ነባር ሀብቶችና ቴክኖሎጂዎች በመፈተሽና በመለየት የግብዓት ማምረቻ ማዕከል (የማምረቻ ክፍሎች) በአዲስ መልክ የማደራጀት ሥራ በመሥራት ግብዓቶች እየተመረቱ ይገኛሉ። ግብዓቶች በዓይነትና በብዛት በማዕከሉ እንዲመረቱ ለማስቻልም የኢንዱስትሪያላይዜሽንና ዲጂታላይዜሽን ሪፎርምም ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በማዕከሉም የተለያዩ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በስፋት ማምረትና ጥቅም ላይ ማዋል በመቻሉ አምስት ሺ የተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ ሥራን ከአሠሪዎች እንዲያገኝ አስችሎታል። በሂደትም ግብዓቶችን በስፋት ማምረት የሚችሉ ተስማሚ የሆኑ የኮንስትራክሽን ግብዓት አምራች ኢንዱስትሪዎች ተለይተው ከውጪ የሚገቡበትና የሚተከሉበትን እድል ፈጥሯል።

ይህንን የግብዓት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን የመትከልና ወደምርት ማምረት የማስገባት ግብ እውን ለማድረግ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በማምረት የዳበረ ልምድ ካለው ራይዚንግ ሆንግፋ ግሩፕ ከተሰኘ የውጪ ኩባንያ ጋር የግብዓት ማምረቻ ፋብሪካዎች ወደ ሃገር ውስጥ ገብተው እንዲተከሉ በቴክኖሎጂ አማራጮችና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት በማድረግ



ኮርፖሬሽኑ ከራይዚንግ ሆንግፋ ግሩፕ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ሲፈራረም

የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሞ ወደሥራ ተገብቷል። በመግባቢያ ሰነዱ የፊርማ ሥነ ሥርዓት ላይ ፋብሪካዎች በአጭር ጊዜ ወደሃገር ውስጥ ገብተው እንደሚተከሉ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

የሚተከሉት ፋብሪካዎች ሥራ ሲጀምሩ ከመሠረታዊ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ውጪ ያሉ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በሃገር ውስጥ አምርቶ ከመጠቀም በተጨማሪ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋለውን የግብዓት አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢንጅነር ዮናስ አያሌው ይገልፃሉ።

በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡ የአልሙኒየም፣ ልዩ ልዩ የኮንክሪት ምርቶችንና ሌሎች የግንባታ ግብዓቶችን በሃገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ከማዳን በተጨማሪ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ግንባታዎችን በጥራት፣ ወጪ ቆጣቢ በሆነና በአጭር ጊዜ ለማከናወን ስለሚያስችል የደንበኞችን እርካታ የበለጠ ለማሳደግ ያስችላል ብለዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ኮርፖሬሽኑ ራሱን የቻለ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረቻ የኢንዱስትሪ ዞን እንዲኖረውም እየተሠራ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ይህን እውን ለማድረግም የተሻለ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፤ የስልጠናና የልህቀት ማዕከል ግንባታ ተጠናቋል፤ የግብዓት ማምረቻ ማዕከል እንደገና የማደራጀት፣ ፋብሪካዎች የሚተከሉባቸው ሕንጻዎች የመገንባትና የግብዓት ማምረቻ ፋብሪካዎችን ለመትከል የሚያግዙ ሌሎች የመሠረተ ልማቶች ግንባታዎች ተከናውነዋል።

ኮርፖሬሽኑ ከተገጣጣሚ ቤቶች ግንባታ በተጨማሪ በዘርፉ የሚስተዋለውን ክፍተት ለመሙላት በሪል ስቴት ልማት የመሠማራት እቅድ ስላለው ግብዓቶች በሃገር ውስጥ መመረታቸው ትልቅ ፋይዳ አለው ብለዋል። አስፈላጊ ግብዓቶች በሃገር ውስጥ መመረታቸውም የውጪ ምንዛሪን ለማዳንና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ለማቅረብና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለመፍጠር ያስችላል።

ከተቋሙ ጋር በጋራ ለመሥራት የውል ስምምነት ያደረገው የራይዚንግ ሆንግፋ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሪታን ሲንግ በበኩላቸው፤ ጎማን መልሶ በመጠቀም፣ የአሉሙኒየም ግብዓቶችን በማምረት፣ የኮንክሪት የግድግዳ ፓኔሎች፣ ቱቦዎችና ሩፍ ታይልስ እንዲሁም በመንገድ ቅብና በሌሎች ተያያዥ የኮንስትራክሽን ግብዓቶት አመራረት ዙሪያ ሰፊ ልምድ ለኮርፖሬሽኑ ከማካፈል በተጨማሪ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች ለኮርፖሬሽኑ ለማቅረብና ከኮርፖሬሽኑ ጋር በጋራ ለመሥራት የደረስነው ስምምነት ውጤታማ እንዲሆን ጊዜ ሳንሰጥ እንሠራለን ብለዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ለማምረት የሚያስችሉ ጥሬ እቃዎች (ሀብቶች) ስላሏት የፋብሪካዎች መተከል ለኮርፖሬሽኑ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ያመለክታሉ። በመጨረሻም በኮርፖሬሽኑ የግብዓት ማምረቻ ማዕከል ፋብሪካዎችን ለመትከል የተዘጋጁ ቦታዎችን፣ የስልጠናና የልህቀት ማዕከሉን ግንባታ፣ የተለያዩ ግብዓቶችን እያመረቱ የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችንና አጠቃላይ የማምረቻ ማዕከሉን የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የዋና መሥሪያ ቤቱን የሥራ ሁኔታ በመጎብኘት አስፈላጊ መረጃዎችን የመለዋወጥ ሥራና ወደ ሃገር ውስጥ ገብተው የሚተከሉ የግብዓት ማምረቻዎች ላይ ስምምነት በማድረግ ውይይቱና ጉብኝቱ ተጠናቋል።

# ዓለም አቀፍ

## የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት የአንዳንድ ሃገራትን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እስከ 50 በመቶ ሊቀንሰው ይችላል

የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት የአንዳንድ ሃገራትን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እስከ 50 በሙቶ ሊቀንስ እንደሚችል የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም ትንበያ አመለከተ፡፡

እንደ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም ገለጻ፣ የዓለም የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን የሚቀጥል ከሆነ የአንዳንድ ነዳጅ አስገቢ ሃገራትን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከ20 እስከ 50 በሙቶ ሊቀንስ ይችላል።

ሁለቱ ሃገራት በምግብ እና የነዳጅ/ኃይል አቅርቦት ከፍተኛ ድርሻ እንደመያዛቸው፣ ጦርነቱ በተለይም አነስተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሃገራት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ካመጣው ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመውጣት የሚያርጉትን ጥረት በማስተጓጎል ላይ ነው።

ጦርነቱ በዋናነት የሚካሄድባት ዩክሬንን ብንመለከት፣ አብዛኛው የሃገሪቱ እርሻ የሚገኘው ከፍተኛ ጦርነት እየተካሄደ በሚገኝባቸው በደቡብ ምሥራቃዊ ክፍሎቿ መሆኑ እና 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬቷ በፈንጂ በመበከሉ የስንዴ ምርቷን ብቻ በ4 ሚሊዮን ቶን ሊያወርደው ይችላል።

በአፍሪካ፣ መካለኛው ምሥራቅ፣ ማዕከላዊ እስያ እና አውሮፓ የሚገኙ አንዳንድ ሃገራት ታዲያ እስከ 75 በሙቶ የሚሆነው ስንዴያቸውን የሚያስገቡት ከነዚህ ሁለት ሃገራት እንደመሆኑ ጉዳቱ ይፀናባቸዋል።

በተለይም በደሃ ሃገራት አብዛኛው የዕለታዊ ገቢያቸውን በምግብ ላይ የሚያውሉ ዜጎች የምግብ ዋጋ በጨመረ ቁጥር የምግብ ፍጆታቸውን ከመቀነስ የዘለለ መፍትሔ ማምጣት በማይችሉበት ቅርቃር ውስጥ ይገባሉ።

የምግብ ዘይትን እንኳን ብናይ ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ ወዲህ የሱፍ ዋጋ በ60 በሙቶ አሻቅቧል።

የዓለማችን 40 በሙቶው የሱፍ ኤክስፖርት እና ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የሱፍ ምርት የምትሸፍነው ዩክሬን ጦርነቱ ከተጀመረ ወዲህ የሱፍ ምርቷ በ95 በሙቶ ወርዷል።

ገበሬዎች ሱፍን የሚዘሩበት ወቅት ላይ ብንገኝም በሃገሪቱ በተከሰተው የነዳጅ እና ማዳበሪያ እጥረት ሳቢያ ሥራዎች መስተጓጎላቸው ሲጠቀስ ዓመታዊ ምርቱም ካለፈው ዓመት አንፃር በ50 በሙቶ እንደሚያሽቆለቁል ተተንብዮዋል።

20 በሙቶውን የሱፍ ምርት ኤክስፖርት በመሸፈን በሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትቀመጠው ሩሲያም ብትሆን የሃገር ውስጥ አቅርቦቷን ለመጠበቅ ስትል ወደውጭ በምትልከው የሱፍ ምርት ላይ ገደብ ጥላለች።

ይህም ከሱፍ ዘይት ባሻገር ሌሎች የምግብ ዘይት ዓይነቶች ዋጋንም ጨምሮታል።

አሁን ላይ የምግብ አቅርቦት ችግሩን ለመፍታት ልዩ ልዩ የመፍትሔ ሐሳቦች እየተሰነዘሩ ሲሆን ከዚህም ሌሎች ዋና ዋና ከክምችታቸውን አውጥተው በማቅረብ ጭምር የሰብል አምራች ሃገራት አቅርቦታቸውን ማሳደግ ይገኝበታል።

በነዳጅም ረገድም እንዲሁ ነዳጅ አምራች ሀገራት አቅርቦታቸውን በማሳደግ የነዳጅ፣ የማዳበሪያ እና የመጓጓዣ ዋጋን መቀነስ መቻል እንዳለባቸው ተመላክቷል።



## ሕንድ ውስጥ በአንድ ሕንጻ ላይ በተነሳ የእሳት አደጋ ቢያንስ 27 ሰዎች ሞቱ

በሕንድ ዋና ከተማ ደልሒ በአንድ ባለአራት ፎቅ የቢሮ ሕንጻ ላይ በተነሳ የእሳት አደጋ ቢያንስ 27 ሰዎች ሲሞቱ፣ በ12 ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን የእሳት እና ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት አስታወቀ።

የእሳት አደጋው ሲነሳ ከ70 ሰዎች በላይ በሕንጻው ውስጥ የነበሩ ሲሆን፣ ፖሊስ የሕንጻውን መስኮቶች በመስበርና ገመድ በመዘርጋት የቀሪ ሰዎችን ሕይወት መታደግ መቻሉ ተነግሯል።የአብዛኞቹ ሟቾች አስከሬኖች የተገኙት በህንጻው ሁለተኛ ፎቅ ላይ ነው ተብሏል።በዋና መዲናዋ ደልሒ በሙንዱካ ባቡር ጣቢያ አቅራቢያ የተነሳውን ይህንን እሳት ለማጥፋት 20 የእሳት ማጥፊያ ተሽከርካሪዎች ተሰማርተዋል።

በሕንጻው ውስጥ የተዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ችግር ለአደጋው መነሻ ምክንያት እንደሆነም ተገልጿል።የሕንድ መገናኛ ብዙኃን ከአደጋው ጋር በተያያዘ ሁለት ግለሰቦች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ዘግበዋል።ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ በአደጋው ምክንያት በደረሰው ጉዳት ማዘናቸውን ገልጸው፣ ለእያንዳንዱ ሟች ቤተሰቦች 200 ሺህ ሩፒ ( 2 ሺህ 580 ዶላር) ካሳ ለመክፈል ቃል ገብተዋል።

እሳቱ ከጠፋ በኋላ የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች ነፍስ የማዳን ሥራቸውን እንደቀጠሉ እና ሰፊ የሆነውን የአደጋውን አካባቢው ለመቆጣጠር ጊዜ እንደሚወስድ ‘ታይምስ ኦፍ ኢንዲያ’ ጋዜጣ የእሳት አደጋ ምክትል ኃላፊ ሰኒል ቾድሃሪን ጠቅሶ ዘግቧል።የአካባቢው ባለሥልጣን ጃጊ ራም ጄን የኤሌክትሪክ ችግር ለእሳት አደጋው መንስኤ እንደሆነ እና ሕንጻው አስፈላጊ የሆኑ የእሳት ደኅንነት ማረጋገጫ እንዳልነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርቶች እንዳመለከቱ ገልጸዋል።”ምርመራ ጀምረናል፤ የማንኛውም ባለሥልጣን ስህተት ከሆነ ተገቢውን እርምጃ እንወስዳለን “ ሲሉ ጃጊ ለ’ሂንዱስታን ታይምስ’ ጋዜጣ ተናግረዋል።




# መልካም ስብዕና ልጆችን

**አስናቀ ፀጋዬ**

ልጆች እንዴት ሰነበታችሁ? ሳምንቱስ ጥሩ አለፈ? ሳምንቱን ትምህርታችሁን በትጋት በመከታተል እንዳሳለፋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆች ስለ ስብዕና ግንባታ ታውቃላችሁ? የስብዕና ግንባታ በመደበኛው ትምህርት ከምታገኙት እውቀት በተጨማሪ ከወላጆቻችሁ፣ ከመምህራኖቻችሁ እንዲሁም ከክፍል ጓደኞቻችሁ መልካም ስነ ምግባርን በመቅሰም የምታገኙት ትምህርት ነው።

ልጆች እናንተ በስነምግባር ታንፃችሁ እንድታድጉና መልካም ስብዕናን እንድታጎለብቱ ታዲያ የወላጆቻችሁና መምህራኖቻችሁ ክትትል ያስፈልጋችኋል። በተለይ ደግሞ ወላጆቻችሁ መጥፎውን ከጥሩ በመለየት የተገባ ባህሪ እንድታሳዩ ሊያስተምሯችሁ ይገባል። በተለይ ደግሞ ከታች የተዘረዘሩትን የልጆች አስር የስብዕና ማጎልበቻ መንገዶችን ቢከተሉ እናንተ ልጆች የተሟላ ስብዕና ይዛችሁ ታድጋላችሁ።

ልጆች፣ ዛሬ ለቤተሰቦቻችሁ አንዳንድ ሀሳቦችን ማካፈል መረጥኩ። እናንተም ብታውቋቸው አይከፋም ብዬ በማሰብ ላጋራችሁ ወደድኩ። መልካም ንባብ።

**1ኛ፡- ለሚያደርጓቸው ነገሮች ጥንቃቄ ያድርጉ**

እንደሚታወቀው ልጆች ብዙ ግዜ ልጆች የሚማሩት ከሚያዩቸው ነገሮች ነው። አብዛኛውን ነገር የሚማሩት ደግሞ ወላጆቻቸው የሚያደርጉትን ነገር በማየት ነው። ከዚህ አንፃር ወላጆች ልጆቻቸው ፊት ለሚናገሩትና ለሚያደርጉት ነገር ጥንቃቄ መውሰድ አለባቸው። በሌላ አባባል ወላጆች ልጆቻቸው ሊያደርጉ የማይፈልጓቸውን ነገሮች እነርሱም ማድረግ የለባቸውም።

**2ኛ፡- ልጆችዎን ማወዳደርና መፈረጅ ያቁሙ**

ወላጆች በማንኛውም መንገድ ልጆቻቸውን ማወዳደርና መፈረጅ የለባቸውም። ልጆች አሁንም ገና ነገሮችን እየተማሩ ያሉበት ደረጃ ላይ በመሆናቸው ወላጆች እነሱን ሲፈርጇቸው በቀላሉ ሊያምኗቸው ይችላሉ። እንደውም አመፀኛና ከዚህም በላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። እነሱን ከሌሎች ልጆች ጋር ማወዳደርም ሞራላቸው እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ ብቁ እንዳልሆኑ እንዲሰማቸውና በራስ የመተማመን መንፈሳቸው እንዲቀንስ ያደርጋል። ስለዚህ ልጆች ቢያጠፉ እንኳን ወላጆች ትክክለኛ ቃላቶችን ተጠቅመው ስህተታቸውን እንዲያርሙ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

**3ኛ፡- በትኩረት ይከታተሉ**

ወላጆች ልጆቻውን በትኩረት ሊከታተሏቸው ይገባል። በተለይ በአሁኑ ግዜ ልጆች ስልኮችና ላፕቶፖች ከእጃቸው ስለማይጠፉ በኢንተርኔት አማካኝነት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች በቅርበት መከታተል ያስፈልጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ልጆች አዘውትረው የሚያደርጓቸውን ነገሮች፣ ፍላጎታቸውንና ልምዳቸውን መከታተል የግድ ይላል። ከክትትሉ ባለፈ ታዲያ ልጆች አዳዲስ ነገሮችን እንዲማሩና እንዲያውቁ ማበረታታት ያስፈልጋል።

**4ኛ፡- ጥሩ አድማጭ ይሁኑ**

ወላጆች በሥራ መብዛትና በተለያዩ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ለልጆቻቸው በቂ ግዜ ሲሰጡ እምብዛም አይታዩም። ከዚህ አንፃር ወላጆች በየትኛውም አጋጣሚ ለልጆቻቸው የተወሰነ ግዜ ሊሰጡ ይገባል። ይህም ልጆች ስለራሳቸው ለመናገርና ለመግለፅ አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል። ወላጆችም የልጆቻውን ችግር ሰምተው ሊያግዟቸው ይገባል። በዚህ ግዜ ታዲያ ልጆች በወላጆቻቸው በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያድርባቸው ያደርጋል።

**5ኛ፡- በሚጠብቁት ልክ ልጆችዎን አይጫኗቸው**

አብዛኞች ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖራቸው ይጠብቃሉ። ይሁንና ወላጆች ልጆቻቸው እንዲሆኑላቸው በሚጠብቁት ልክ ጫና የሚያሳድሩባቸው ከሆነ ከፍተኛ ጫና ውስጥ ገብተው ጫናን መሸከም ባለመቻላቸው አመፀኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ወላጆች ልጆቻቸው መሆን የሚፈልጉት ነገር ላይ ማተኮር ውጤታማ እንዲሆኑ



ማገዝ ይጠበቅባቸዋል። አቅማቸውን በመለየት እነርሱን መንከባከብና ማበረታታም ይገባቸዋል።

**6ኛ፡- ደምቦች ያውጡላቸው**

ልጆችዎን ገና በትንሽነታቸው በኃላፊነት ያሳድጓቸው። ይህም የተፈላጊነትና የሥነሥርዓት ስሜት በውስጣቸው እንዲያድር ያደርጋል። ለዚህም ልጆች ሊከተሏቸው የሚገቡ ደምቦችን ያውጡላቸው። ለምሳሌ ለእንቅልፍ ወደ አልጋ የመሄጃ ሰዓት ያብጁላቸው። በየዕለቱ ጥርሳቸውን የሚያፀዱበትና የሚያጠኑበትንም ሰዓት ያስቀምጡላቸው። እንዲዝናኑ እና የራሳቸውን አስደሳች ጊዜ እንዲያሳልፉ ያድርጉ። ነገር ግን መከተል ያለባቸውን አንዳንድ ደንቦች ማወቅ እንደሚኖርባቸው ያሳውቋቸው።

**7ኛ፡- የስክሪን መመልከቻ ግዜን ይገድቡ**

በዚህ ግዜ ለወላጆች ፈተና እየሆኑ ከመጡ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የልጆች በቲቪ፣ ታብሌትና ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ስክሪኖች ላይ መጠመድ ነው። የዚህ ዘመን ልጆች ትልቁ ሱስም በእነዚሁ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች መለከፍ ነው። በተለይ ደግሞ ልጆች እነዚህን መሳሪያዎች ተከልክለው እንዲያጠኑ ከተደረጉ በኋላ ዳግም ሲመለሱ ቆይታቸው ይጨምራል። ከዚህ አኳያ ወላጆች ልጆች በታብሌቶች፣ ቲቪና ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ላይ የሚኖራቸውን ቆይታ በሰዓት ሊገድቡና ቁጥጥርም ማበጀት ይኖርባቸዋል። ልጆች እነዚህን መሣሪያዎች በሚጠቀሙበት ግዜም ከትምህርት፣ ለልጆች ከሚሆኑ መዝናኛዎችና ከቤተሰብ ጋር ሊያገኙ ይገባል።

ልጆች ሁል ግዜ በቪዲዮ ጌሞች ላይ ብቻ እንዳያሳልፉ ወላጆች አንዳንድ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉና ከስክሪን ውጪ ያሉ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል።

**8ኛ፡- ምሳሌ ይሁኑ**

‹‹የምታወራውን ሆነህ ተገኝ›› እንደሚባለው ወላጆቻቸው ልጆቻቸው የሚጠይቋቸውን ነገሮች ማድረግ አለባቸው። በተለይ ደግሞ በአነስተኛ የዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ልጆች ወላጆቻቸውን ያሚያደርጉትን ሁሉ ያስመስላሉ። ወላጆች የሚያወሯቸውን ነገሮች በድርጊት ካልፈፀሙና ደምብ ካላስቀመጡ ልጆች ይህን ከቁም ነገር ላያስገቡት ይችላሉ። ስለሆነም ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም ባሕሪ ማሳየትና በዚሁ መንገድ እነርሱም ተቀርጸው እንዲያድጉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

**9ኛ፡- ራስ መቻልን ያበረታቱ**

ልጆችን በእንክብካቤ ማሳደግ የወላጆች ግዴታ ነው። ይህ ግን እስከዘላለሙ ሊቀጥል የሚችል ተግባር አይደለም። ምክንያቱም ልጆች አንድ ቀን ነገሮችን በራሳቸው ማድረግ መፈለጋቸው ስለማይቀር ነው። ስለሆነም ልጆች ከወላጆች ርዳታ እንዲላቀቁ ሁሌም በወላጆች ላይ እንዲንጠላጠሉ ማድረግ አያስፈልግም። ልጆች አንዳንድ ነገሮችን በራሳቸው እንዲያከናውኑና እንዲያስተናግዱ ማድረግም ተገቢ ነው። ይህም የኃላፊነት ስሜትን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል።

**10ኛ፡- የወላጅነት ክህሎትዎን ይከልሱ**

ወላጆች ከላይ የተደረደሩትን መፈፀም ብቻ ሳይሆን የወላጅነት ክህሎታቸውንም መከለስ ይኖርባቸዋል። ወላጆች በልጆቻቸው ባህሪ ወይም በሚሰጡት ምላሽ ምክንያት ስህተት የሰሩበት ግዜና ሊቀየሩት የሚችሉት ነገር ሊኖር ይችላል። ለዚህም ወላጆች ግዜ ወስደው የወላጅነት ክህሎታቸውን መከለስና ማሻሻል ይኖርባቸዋል።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ መሐንዲስ


**ብርሃን ፈይሳ**

በኦሊምፒክ፣ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና እና ሌሎች ውድድሮች ላይ የሃገራቸውን መልካም ገጽታ የገነቡ ድንቅ አትሌቶች የጀርባ አጥንትና የውድድር መሐንዲሶች አሰልጣኞቻቸው ናቸው። ኢትዮጵያ ደግሞ ምርጥና ዓለምን ያስደመመ ብቃት ያሳዩ አትሌቶችን ብቻ ሳይሆን፣ በልምድና በእውቀት አንቱ የተሰኙ አሰልጣኞችንም ማፍራት የቻለች ሃገር ናት።

በመላው ዓለም አድናቆትና ከበሬታን ካገኙ ኢትዮጵያውያን የአትሌቲክስ አሰልጣኞች መካከል ደግሞ ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ ከቀዳሚዎቹ መካከል ይሰለፋሉ። እኚህ ታላቅ አሰልጣኝ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ግንቦት 7 ቀን 2008 ዓ.ም በዛሬው እለት ነው፤ የዛሬው የአዲስ ዘመን ስፖርት ማህደርም እኚህን ታላቅ የአትሌቲክስ ባለውለታ ሊያስታውስ ወዷል።

አሰልጣኝ ወልደመስቀል ኮስትሬ በ1939 ዓም በሰሜን ሸዋ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ልዩ ስሙ ወንፈስ በተባለ ስፍራ ከአባታቸው አቶ ኮስትሬ ሰበሬ እና ከእናታቸው ወይዘሮ እናትገብርኤል ደስታ መወለዳቸውን በሕይወት ታሪካቸው ላይ ተሰንዷል። በትውልድ ስፍራቸው የቤተክህነት ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በቀንና ማታ መርሐ ግብር ዘመናዊ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከትምህርት ጎን ለጎን በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩት የያኔው ታዳጊ ወልደመስቀል ከእግር ኳስ በተጨማሪ በ400፣ 800 እና 1ሺ500 ሜትር ውድድሮች ተካፋይ ነበሩ።

የስፖርት ፍቅር የሰረጸባቸው አሰልጣኙ በስፖርቱ ትምህርትም ገፍተው በመቀጠል ከመምህራን ማሰልጠኛ በስፖርት መምህርነት ተመርቀዋል። በመምህርነት ሙያ ላይ እያሉም ከሃንጋሪ ነጻ የትምህርት እድል በማግኘታቸው ወደዚያው አቅንተው በአካዳሚክስ ሳይንስ በምርምርና



**አሰልጣኝ ወልደመስቀል ኮስትሬ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ላይ ያሳረፉት አሻራ ሁሌም እንዲታወሱ ያደርጋቸዋል፤**

ጥናት የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

ወደ ሃገራቸው ተመልሰውም በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ እንዲሁም በወቅቱ በነበረው የአካል ማሰልጠኛና ስፖርት ኮሚሽን ሠርተዋል። የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን ረዳት አሰልጣኝ በመሆን የሚወዱትን ስፖርት በ1970ዎቹ የተቀላቀሉት አሰልጣኙ፣ ስማቸውን ከመቃብር በላይ ያዋሉ በርካታ ገድሎችን በመፈጸም ሃገራቸውንም ጭምር አኩርተዋል።

አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባን ተክተው ለሶስት አሥርት ዓመታት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን አሰልጣኝ በመሆን ያገለገሉት አሰልጣኙ፤ በዓለም አደባባይ ማንጸባረቅ የቻሉትን ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ፣ ስለሺ ስህን፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ታሪኩ በቀለ፣ ገብረእግዚአብሄር ገብረማርያም እና ጥሩነሽ ዲባባን የመሳሰሉ አትሌቶች አፍርተዋል።

ከውጤታማነታቸው ባለፈ በአሰልጣኝነት ዘመናቸው በተለይ የሚታወቁት በስነምግባር የታነጹ አትሌቶችን በማውጣት ነው። በሙኒክ ኦሊምፒክ በረዳትነት እንዲሁም በአምስት ኦሊምፒኮች በዋና አሰልጣኝነት (ባርሴሎና፣ አትላንታ፣ ሲድኒ፣ አቴንስ እና ቤጂንግ) ኦሊምፒኮች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን መርተዋል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ካስመዘገበቻቸው 58 ሜዳሊያዎች ውስጥ 28ቱን (13 የወርቅ፣ 6የብር እና 9 የነሐስ ሜዳሊያዎች) ማስመዝገብ የተቻለው በእሳቸው የአሰልጣኝነት ዘመን ነው። በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ ትልቁ የሜዳሊያ ቁጥር በተመዘገበበት የሲድኒ ኦሊምፒክ (4የወርቅ፣ 6 የብር እና 8 የነሃስ በጥቅሉ 8 ሜዳሊያዎች) ድል ላይም አሰልጣኙ ከፍተኛ ሚና በታሪክ ይዘከራል።

አሰልጣኝ ወልደመስቀል በስምንት የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች ላይም በዋና አሰልጣኝነት ተሳትፈዋል። በተለይ የሚታወቁትና በአትሌቲክስ ስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ አክብሮትን ያገኙት ደግሞ ኢትዮጵያ በተለይም በምትታወቅበት የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር አትሌቶችን ለውጤት በማብቃታቸው ነው።

‹‹የኢትዮጵያ አትሌቲክስ አርክቴክት›› የሚሰኙት እኚህ ታላቅ አሰልጣኝ ታላቅነታቸውን የሚመሰክሩት ኢትዮጵያውያን እና አፍሪካውያን ብቻ አይደሉም፤ መላው ዓለምም ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ደግሞ እአአ በ2006 በዓለም አቀፍ ደረጃ ያገኙት የዓመቱ ምርጥ አሰልጣኝነት ሽልማት ነው። በዓለም አትሌቲክስ የሚዘጋጀውን ይህንን ሽልማት በመቀዳጀት ብቸኛው ኢትዮጵያዊ አሰልጣኝም ናቸው።

አሰልጣኝ ወልደመስቀል ኮስትሬ ከ1970ዎቹ አንስቶ ለኢትዮጵያ ታላቅ ክብርን ባጎናጸፈው የአትሌቲክስ ስፖርት በዋና አሰልጣኝነት እስከ 2008ዓ.ም አገልግለዋል። አሰልጣኙ በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ለረጅም ጊዜ በውጪ እና በሃገር ውስጥ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው፣ በዛሬው ዕለት ግንቦት 07 ቀን 2008 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የቀብር ሥነሥርዓታቸውም አትሌቶች፣ የስፖርቱ ባለሙያዎች፣ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዲሁም የስፖርቱ ወዳጆች በተገኙበት በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።